

# ትንሣኤ



በድሬዳዋ የጥንቱ ሰማይ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን

የጥርና የየካቲት ወራት ፲፱፻፹፫ ዓ.ም.

ቁጥር ፩፻፵፯



በጋሞጐፋ ሀ/ስብከት የጸርጊ ቅ/ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን

ዋጋው ፩ ብር

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»


ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ
ም አዘጋጅ መ/ክንፈ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና
ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።



የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፡


# ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ርእስ አንቀጽ (ከእግዚአብሔር ተምራችኋል) | ፪ |
| ቅዱስነታቸው ያስተላለፉት ቃለ ቡራኬ | ፬ |
| የሰላም አገርዋ ወዴት ነው ? | ፮ |
| ዜና ሊቃውንት | ፰ |
| የቤተ ክርስቲያን ታሪክ | ፱ |
| በሰሜን ሸዋ የምትገኘው የግፍት ማርያም ታሪክ በአጭሩ | ፲፩ |
| በጥምቀት ሁለተኛ ልደት | ፲፫ |
| አስደናቂ ተአምር | ፲፭ |
| ዜና ዕረፍት | ፲፮ |
| እናስተዋውቃችሁ | ፲፯ |
| የሴቶች ዓምድ | ፳ |
| ጾማችሁ እንደ ግብዞች አይሁን | ፳፩ |
| ሒዱና አስተምሩ | ፳፫ |
| ጤናችን | ፳፬ |

## ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጆች

ከሁሉ አስቀድሜ በጌታችን በመድኃኒታችንና በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላምታ አቀርባለሁ የትንሣኤን መጽሔት መከታተል ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ጠቃሚ ትምህርትን አግኝቸበታለሁ ።

በተለይ ደብዳቤዎች በሚለው ክፍል በትምህርት ሰጭነቱ ከፍተኛ ጥበብ ይገኝበታል በአጠቃላይ መጽሔቱ በትምህርት ሰጭነቱ ብቻ ሳይሆን በአቀራረቡም አንባብያንን የመሳቡ ሁኔታ ከፍተኛ ነው ። ዛሬም ብዕሬን አንስቸ ለሥነ ጽሑፍ ተሰታፊ እንድሆን ስላደረገኝ ከዚህ በታች የማቀርባቸውን ጥያቄዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሲሆን ለጥያቄዬ መልካም መልስ ትመልሱልኝ ዘንድ እጠይቃለሁ ።

፩ኛ/ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ። እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ማቴ ፳፰—፲፱ ።

በሐዋርያት ሥራ ደግሞ ጴጥሮስ ንሥሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሠረይላችሁ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ ይላል ፪—፴፰— ፴፱ ስለዚህ እንደ ጴጥሮስ አባባል ከሶስቱ አካላት የወልድን ስም በመጥራት ብቻ ማጥመቅ ይቻላልን? ካልተቻለስ ጴጥሮስ እንዴት እንዲህ ሊል ቻለ ይህ እንዲገለጥልኝ ።

፪ኛ/ በምድር ላይ ሰላመን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ ሰይፍን እንጂ ወንድ ልጅን ከአባቱ ሴት ልጅንም ከእናትዋ ምራትንም ከአማትዋ እለይ ዘንድ መጥቻለሁና ይላል ማቴ ፲— ፴፬·፴፭ ይህ ቃል ምን ማለት ነው ።

፫ኛ/ አሁን ግን በሚሻል የተስፋ ቃል በተመሠረተ በሚሻል ኪዳን ደግሞ መካከለኛ እንደሚሆን በዚያ ልክ እጅግ አገልግሎት አግኝቷል ። ፊተኛው ኪዳን ነቀፋ ባይኖረው ለሁለተኛው ሥፍራ ባላስፈለገም ነበር እነሱን እየነቀፈ ይላቸዋልና እንሆ ከእሥራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት አዲስ ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ይላል ይህንን አብራርታችሁ እንድትመልሱልኝ መልሳችሁን እጠባበቃለሁ ። ሰሎሞን ተፈራ ኢሉባቦር አስተዳደር አካባቢ ።

### መልስ

ሰሎሞን ተፈራ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስላቀረብከልን ሰላምታ እኛም አፀፋውን በመመለስ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ ካንተ ጋይ ይሁን እንላለን ያቀረብካቸውንም ጥያቄዎች ከዚህ እንደሚከተለው እንመልሳለን ።

፩ኛ/ ጌታ ሐዋርያትን በዓለም ዙሪያ እንዲያስተምሩና በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ ማዘዙ በማቴዎስ ወንጌል ፳፰—፲፱ ተገልጾአል ስለዚህ ጌታ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ካለ ሐዋርያ ጴጥሮስ እንዴት በኢየሱስ ስም ተጠመቁ አለ ስለምትለው ክርስቶስ ሰው እንዲሆን የሰውን ሥጋ እንዲለብስ ነቢያት ትንቢት ተናግረውለት ነበር በተነገረውም ትንቢት መሠረት ከሰማይ ወርዶ ከእመቤታችንም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍስዋ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሆነ በዚህም ዓለም ወንጌልን አስተምሮ በእሱ ያመነ እንደሚድን በእሱ ያላመነ ግን እንደሚጐዳ አስተምሮአል ዮሐ ፫—፲፰ ።

በዮሐንስ እጅ የተጠመቀውም ኃጢአታችንን ለማስተሥረይ ነው እንጂ እሱ ኃጢአት ኑሮበት አይደለም ከዚህም የተነሣ ስለኛ በመስቀል ተሰቅሎ መንፈሳዊ ነፃነታችን ካጐናጸፈን በኋላ ሐዋርያትን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው ሲል አዝዧቸው ወደ ሰማይ አርጓል በትእዛዙም መሠረት ሐዋርያት በኢየሱስ ክረስቶስ ስም እመኑ ብለው በማስተማር የወንጌልን ትምህርት ለዓለም ሲያዳርሱ ችለዋል ።

ያንተ ጥያቄ ግን ጴጥሮስ ለምን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምናችሁ ተጠመቁ አላለም ለምን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብቻ አለው የምትለው ማንኛውም ሰው ሲጠመቅ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ተብሎ ነው የሚጠመቀው እንጂ በስመ ወልድ ተብሎ የሚጠመቅ አይገኝም ።

ቅዱስ ጴጥሮስ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ ማለቱ ሕገ ወንጌለን የሠራ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እንዲህ ሲሆን ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ የተለየበት ሰዓት ደቂቃ ሰኮንድ የለም

ወደ ገጽ ፫ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

(ርእሰ አንቀጽ)

# "ከእግዚአብሔር ተምራችኋል"

የትምህርት ዓይነቱ እጅግ በጣም ብዙ ስለሆነ በቁጥር ተወስኖ ሊነገር አይችልም በቃል በመነጋገር በጆሮ በመስማት በዓይን በማየት አብሮ በመኖር በመሳሰሉትም አንዱ ከሌላው የሚማረው ትምህርት አለው ፡ ይሁን እንጂ ዋና ዋናዎቹ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ተከፍለው ይነገራሉ ከእነርሱም አንደኛው መንፈሳዊ ሲሆን ሁለተኛው ሥጋዊ ነው ሁለቱንም በቀደም ተከተል እንመለከታቸዋለን ።

## ሀ· ሥጋዊ ትምህርት

በሥጋዊ ትምህርት በኩል ተመድበው የሚነገሩት እርሻ ቁፋሮ ፡ ንግድ ፡ ጽሬት ፡ ድጉሰት ፡ ጸናጽል ፡ ከበሮ ፡ ውኃ ዋና ፡ ፈረስ ግልቢያና የመሳሰሉትም ሲሆኑ በየዘመኑ የሚፈለሰፉትንም ጥበባት ያጠቃልላሉ ።

## ለ· መንፈሳዊ ትምህርት

ከመንፈሳውያን ትምህርቶች የመጀመሪያውን ደረጃ የሚይዘው ሃይማኖት ነው "አሚንስ መሠረት ይዕቲ ወካልዓኒሃ ሕንፃ ወንድቅ እሙንቱ" ሃይማኖት መሠረት ናት ሌሎች ምግባራት ደግሞ እንደ ግድግዳና እንደጣራ ናቸው ብለው ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንት እንደተናገሩት ፡ ማንኛውም ክርስቲያን እምነቱን ከሁሉም ሥነ ምግባራት በማስቀደም ሊፈጽማቸው የሚገቡ ጾም ጸሎት ስጊድ ምጽዋት ፡ ትሕትና፡ ፍቅር ፡ ሰላም ፡ አንድነትና የመሳሰሉትም ናቸው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሰው ሆኖ ከእመቤታችን ድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ያደገው የዕብራውያንን ሕግ እየተማረ ቀስ በቀስ ነው ፡ ከኃጢአት በስተቀር በሰዎች ላይ የደረሰውን ችግርና ደስታ ተሳትፎአል ፡ ወደ ሠርግ ቤት ሄዶ ውኃውን ጠጅ በማድረግ የተቸገረውን ሙሽራ ረድቶታል ወደ ኃዘን ቤት በመሄድም ወንድማቸው አልዓዛር ሞቶባቸው ሲያዝኑ ሲያለቅሱ የነበሩትን ማርታንና ማርያምን የማጽናኛ ትምህርት ካስተማራቸው በኋላ የሞተውንም አሥነሥቶ አገናኝቷቸዋል ። ጌታችን ከተጠመቀ በኋላ ሳይውል ሳያድር ወደ ገዳም ለመጾም እንደ ሄደ የታወቀ ነው ፡ በሚጾምበት ጊዜ ሰይጣን በልዩ ልዩ መንገድ ሊፈትነው ቀርቦ ነበር ፡ ጌታችን ግን በስስት የመጣውን በትዕግሥት ፡ በትዕቢት የመጣውን በትሕትና በፍቅረ ንዋይ የመጣውን ሰይጣን በጸሊአ ንዋይ ድል ነሥቶ ድራሹን አጥፍቶታል ። ከዚያም በኋላ አይሁድን በተንኮል አነሣሥቶ በዕለተ ዓርብ እስከሚያሰቅለው ድረስ ለመፈታተን በሌላ መንገድ እንዳልቀረበ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አስተምረውናል ።

በዚህም ሦስት ነገሮችን አስተምሮናል እነርሱም ትዕግስት ፡ ትሕትና ገንዘብን አለመውደድ ናቸው፡ እነዚህን አዘውትረው የሚፈጽሙ ሰዎች ከጌታችን ከመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተማሩ ናቸውና ማንም ሊያሸንፋቸው አይችልም ።

እግዚአብሔር አምላክ በመጀመሪያ የፈጠረው መላእክትን ነው ፡ ከመላእክትም መካከል እጅግ በጣም ቀራቢና አሐዜ መንጦላዕት አድርጎ የፈጠረው ሳጥናኤልን ነበር ነገር ግን በተሰጣቸው አዕምሮ ተመራምረው ይወቁኝ ብሎ ለጥቂት ጊዜ ቢሠወራቸው ሳጥናኤል ፈጣሪውን ዘንግቶ በማምለክ ፈንታ አምልኩኝ በማመስገን ፈንታ አመስግኑኝ ስላለ ከመዓርገ ወደቀ ፡ ከክብሩ ተዋረደ ፡ በእርሱም ፈንታ ፈጣሪውን የሚያመሰግን ሰው ተፈጠረ ።

ሰውም ከተፈጠረ በኋላ በተወደደችውና በአማረችው ምድረ ገነት ሲቀመጥ ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ላሉት ፍጥረታት ሁሉ የበላይነት ነበረው የበላይነቱንም ሥልጣን እንደያዘ በገነት የኖረው ለሰባት ዓመታት ብቻ ነው ፡ ከዚያ በኋላ ከፈጣሪው የታዘዘውን ትእዛዝ በማፍረሱ እንደመጀመሪያው መስሐቲ ሳጥናኤል ከመዓርገ ወደቀ ከክብሩም ተዋረደ ከገነትም ወጥቶ ተባረረ ይሁን እንጂ ማንም ሳያስተምረው በፈታሒነቱ አንጻር መሐሪነቱ እንዳለ ተመራምሮ አውቆ ቢያዝንና ቢያለቅስ ከሰማየ ሰማያት ወርጀ ከድንግል ማርያም ተወልጀ ተሰቅዬ ሙቼ ተነሥቼ ሥጋየን ቆርሼ ደሚን አፍስሼ አድንሃለሁ

የሚል ተስፋ ከፈጣሪው ተሰጠው ።

ይህ የተሰጠው የተስፋ ቃል የሚፈጸምበት ዘመን በጣም ሩቅ ቢሆንም በየዘመኑ የሚነሡ አበው በቃል እያስተማሩ ስላለፉ የተነገረው የተስፋ ቃል ሳይዘነጋ ከሙሴ ደርሷል በሙሴ ዘመን በጽሑፍ ላይ ሰፍሮ ሁሉም ይማረውና ተምሮም ያስተምረው ጀመር ስለዚህም አለማወቅ እየተወገደ የእግዚአብሔር አዳኝነት በሰፊው ለመነገር በቅቷል ይህንንም ነቢዩ ኤርምያስ ሲገልጽ "እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን እያንዳንዱም ወንድሙን አግዚአብሔርን ዕወቅ ብሎ አያስተምርም ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉም ያው ቁኛል " ብሏል እንዲሁም ከደቂቀ ነቢያት አንዱ ዕንባቆም "ውኃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ ትሞላለች" ብሎ ተናግሯል" ኤር· ፴፩/፴፬ ዕንባቆም ፪ ፡ ፲፬ ።

በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ እግዚአብሔር አምላክ ሰዎችን በልዩ ልዩ መንገድ አስተምሯል፡ ከስሕተትም መልሷል ፡ ነገር ግን ሰምተው እንዳልሰሙ ፡ ዓይተው እንዳላዩ የሚሆኑ ሰዎች በብዛት ስለሚገኙ መምህራን እንደሌሉና መጻሕፍትንም እንደማይተረጉሙና እንደማያስተምሩ አድርገው የሚገምቱ ሰዎች ጥቂቶች አይደሉም ።

በተለይ በዘመነ ሐዲስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አብሮ በመዋልና በማደር አብሮ በመብላትና በመጠጣት እንዲሁም እንደ ሰዎች በመራብና በመጠማት ከኃጢአት በስተቀር በማንኛውም ማኅበራዊ ኑሮ በመሳተፍ ማስተማሩ ከላይ ተገልጿል ።

ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ እናንተ ራሳችሁ እርስ በእርሳችሁ ልትዋደዱ ከእግዚአብሔር ተምራችኋልና ስለወንድማማች መዋደድ ማንም ይጽፍላችሁ ዘንድ አያስፈልጋችሁም ሲል ተናግሯል ፡ ይኸው ሐዋርያው በተጨማሪ ለዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ "ከጥንት ጀምሮ እግዚእብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዘመናትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን (አስተማረን) ብሏል ።

ከአብ የባርይ ልጅ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ያልተማርነው ትምህርት አይገኝም ከላይ እንደተመለከትነው ፍቅርን ፡ ትሕትናን ፡ ሰላምን ፡ አንድነትን ፡ ትዕግሥትን ፡ ጾምን ጸሎትን ፡ ስግደትን ፡ ምጽዋትንና የመሳሰሉትን ሥነ ምግባራት ተምረናል የተማርናቸውን መንፈሳውያን ትምህርቶች በሥራ ባንተረጉማቸው የምንጐዳው ራሳችን ነው እንጂ ሌላውን አይደለም ።

ጌታችን መጽኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዛሬ ድረስ ስለአደረገልን ቸርነት እያመሰገን ወደፊት የሚያደርግልንን ቸርነት በትዕግሥት መጠበቅ ይኖርብናል በእግዚአብሔር የሚያምን ከእርሱም የተማረ ሁሉ የሚፈልገው ነገር ሁሉ ይፈጸምለታል ።

በአሁኑ ጊዜ ዓለም በጥበብ እጅግ በጣም ተራቀል ወደታች በርባሮስን ወደ ላይ ዓለም መላእክትን ዓየን ከሚልበት ደረጃ ደርሷል ማወቁ መራቀቁ መመራመሩ በፈጣሪ ዘንድ ባልተጠላም ነበር ነገር ግን ከጉኑ ካሉት ሰላምና ፍቅር የሚተዋወቀ መስሎ አይታይም ዓይን ካፍንጫና ከጆሮ መካከል ተፈጥሮ እነርሱን ለማየት እንደማይቻለው ዓለምም የሩቁን እንደሚመለከት በምድር ከአጠገቡ ከሚገኙት ደጋግ ነገሮች ቢተዋወቀ ከእግዚአብሔር የተማረ መሆኑን ያረጋግጥ ነበር ።

ከእግዚአብሔር ያልተማረ ሰላም የለውም ከእግዚአብሔር ያልተማረ ፍቅርና አንድነት አይኖረውም ከእግዚአብሔር ያልተማረ ትዕግሥት አይኖረውምና ሁሉም ዓለም የእግዚአብሔር ደቀ መዝሙር ይሁን እንላለን ።

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፩ የዞረ)

ስለዚህ በኢየሱስ አምናችሁ ተጠመቁ ቢል አንድ ነው ዋናው መመልከት ያለብህ ኢየሱስ ያዘዘውን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ያለውን ነው ቅዱስ ጴጥሮስ በኢየሱስ ስም አምናችሁ ተጠመቁ ቢል የሚያስነቅፍ አይደለም ከዚህም ሌላ የሐ· ፩—፲፱ የሐ ፱—፲፩ የሐ ፲፬—፩ መመልከት ነው አብ በወልድና በመንፈስ ቅደስ ወልድም በአብና በመንፈስ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስም በአብና በወልድ ህልው ነው ።

፪ኛው በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ ስላልከውም ሃይማኖትን ያመለክታል ይህም ወላጆች በእግዚአብሔር አማኞች ሲሆኑ ልጆቻቸው ይከዳሉ ፣ ልጆች ሲያምኑ ደግሞ ወላጆች ይከዳሉ ስለዚህ ወላጆችና ልጆች በሃይማኖት አንድ ሆነው ካልተገኙ በሃይማ

(ወደ ገጽ ፲ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ልደት ምክንያት በማድረግ ያስተላለፉት ቃለ ቡራኬ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ፤ በገጠርና በከተማ የምትገኙ ምእመናን የሀገራችንን ዳር ድንበር ለማስከበር ነፃነትዋንና አንድነትዋን ለመጠበቅ በመሐል አገር በጠረፍ በየብስና በባሕር በሥራ የምትገኙ ሠራዊት! በሕማም ምክንያት በሐኪም ቤት ያላችሁ ምእመናን

የዓለም ቤዛ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን ለብርሃነ ልደቱ በሰላም አደረሳችሁ ።

"ኢትፍርሁ እስመ ናሁ እዜንወክሙ ዐቢየ ዜና ፍሥሐ ዘይከውን ለክሙ ወለኩሉ ዓለም እነሆ ለእናንተና ለዓለም ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችሁአለሁና አትፍሩ" (ሉቃ. ፪፡፲፩)

የሰው ልጅ በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ከፈጣሪው በመራቁ ፈጣሪውም ከርሱ በክብርና በረድኤት በመለየቱ በፍርሃት መኖር ጀመረ፡ መንፈሳዊ ሕይወቱ ጨለመ ደስታው ወደ ኀዘን ተለወጠ ፤ ከፈጣሪውና ከባልንጀራው ጋር ሰላምን አጣ ፤ ስለዚህ ሥጋዊውም ሆነ መንፈሳዊው ሕይወቱ ጥላቻን የተመላ ሆነ ፤ ከእግዚአብሔርም ከሰውም ጋር ስምምነትን ሊያገኝ አልቻለም "ኃጢአት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል እንደ መጋረጃ ሆኖአልና" (ኢሳ. ፶፱፡፩ ፪)

ነገር ግን የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ሰላምና ደስታን አጥቶ በፍርሃትና በጨለማ ተውጦ ለዘለዓለም እንዲኖር እግዚአብሔር አልፈቀደም ። ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ እንደሚያድነው ተስፋ ሰጠው ። የተስፋው ዘመን ፍጻሜም በደረሰ ጊዜ በበደሉ ምክንያት ከተፈረደበት ፍዳ ነፃ ያወጣው ዘንድ እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆኖ ተወለደ ። በተወለደበትም ዕለት በቤተ ልሔም አካባቢ መንጎቻቸውን ይጠብቁ ለነበሩ እረኞች የእግዚአብሔር መልአክ



ቅዱስነታቸው ቃለ ቡራኬ ሲያስተላልፉ

"አትፍሩ ለእናንተና ለዓለም ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ እነግራችሁ አለሁና" በማለቱ የክርስቶስ ልደት ለዓለም ታላቅ ደስታ መሆኑን ፤ በክርስቶስ ልደት በሰው ልጅ መንፈሳዊ ሕይወት ላይ የነበረው ፍርሀት መወገዱን አብስሮአል ።

ከመልአኩም ጋር የነበሩ የሰማይ ሠራዊት ከሰዎች ጋር በኅብረት "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ ክብር ለእግዚአብሔር በሰማያት ይሁን ፤ ሰላም በምድር፡፡ ለሰውም በጎ ፈቃድ ይሁን" ብለው በመዘመራቸው በክርስቶስ ልደት በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ሰላም መመሥረቱን ፤ ዕርቅ መጀመሩን ከፈጣሪው ርቆ የነበረው የሰው ልጅ ወደ ፈጣሪው መቅረቡን መስክረዋል ።

እንደዚሁም "ሕዝብ ዘይነብር ውስተ ጽልመት ርእየ ብርሃነ ዐቢየ ፤ ወለእለሂ ይነብሩ ውስተ ጽልመት ወጸላሎተ ሞት ብርሃን ሠርቀ ሎሙ በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ ፤ በጨለማና በሞት ጥላ ውስጥ ለሚኖሩም ብርሃን ወጣላቸው" ተብሎ በነቢዩ ኢሳይያስ አስቀድሞ እንደተነገረ እውነተኛው የዓለም ብርሃን ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በመምጣቱ ከሰው ሕይወት ላይ የኃጢአትና የሞት ጨለማ ተወገደ (ኢሳ. ፱፡፩—፬) የሰው መንፈሳዊ ሕይወት ብሩህ ሆነ በክርስቶስ ብርሃነ ልደት ሰው እግዚአብሔርን ለማየት ቻለ በክርስቶስ ልደት መላእክትና የሰው ልጆች አንድ ማኅበር ሆኑ ፤ በአንድ ድምፅም እግዚአብሔርን አመሰገኑ በአንድ ቃል ሰላምን ለዓለም ዐወጁ ፤ ለሰውም በጎ ፈቃድን ተመኙ ። ስለዚህ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ሰላምና ፍቅር ድኅነትና ደስታ ብርሃንም ነው ። በመሆኑም በዓሉን በምናከብርበት ዕለት እነዚህን ነገሮች ልናስታውስ ይገባል ።

ክርስቶስ በተወለደበት ዕለት የታወጀው የዓለም ሰላም "አትፍሩ" የሚለው አጽናኝ ቃል ዛሬ እንዴት ነው? ዛሬ በዓለም ላይ ደስታ አለወይ? ሰዎች ያለ ፍርሃት መኖር ችለዋል ወይ?

የሰው ልጅ በክርስቶስ ስለተጎናፀፈው ነፃነቱ ምክንያት እየሰጠ እንደገና በራሱ ላይ የኃጢአት ቀንበርን በመጫኑ የሰላም ባለቤት ከመሆን ወጥቶአል ። በሰላምና በነፃነት እንዲኖርባት በተሰጠችው ዓለም ላይም ከሰላም ይልቅ ጥላቻና ጦርነት ፍርሃትና ሽብር ሥጋትና ጭንቀት በዝቶ ይታያል ።

ይሁን እንጂ ሰላም ወዳጆች የዓለም መንግሥታትና የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ሰላምን በዓለም ላይ ለማስፈን ከፍተኛ ጥረት ማድረጋቸው አልቀረም ፤ ነገር ግን "ለክፉዎች ሰላም የላቸውም" ተብሎ እንደ ተጻፈ (ኢሳ. ፶፯፡፳፩) ሰላምንና አንድነትን የማይሹ ከበጎ ነገር ይልቅ ክፋትን የሚከተሉ የሰላም ተቃዋሚዎች በየጊዜው በመነሣታቸው በሰው ልጆች መካከል ጥላቻ ገኖ ፤ ጦርነት ሰፍኖ ሰላም መንምኖ ይታያል ። ይህም ሁኔታ ሰላም አፍቃሪዎችን ሁሉ እያሳዘነ ነው።

ዛሬ ያለንበት ዘመን የሰው ልጅ በጥበብ ተራቆ ፤ በዕውቀት መጥቆ የሚገኝበት ወቅት ሲሆን በዚሁ አንጻር ደግሞ የከፍተኛ ጥፋት ባለቤት ሆኖ መገኘቱ እጅግ አሳዛኝ ነው ። በተለይም በአሁኑ ወቅት እጅግ አስጊና አስቃቂ የሆነው በፋርስ ባሕረ ሠላጤ ላይ የተመዘዘው ሰይፍ በሰላም ወደ አፎቱ እንዲመለስ ካልተደረገ በአካባቢውና በሌላውም ላይ የሚደር ሰው ጥፋት ከዚህ በፊት በዓለም, ላይ ከታየው ጥፋት ያላነሰ እንደሚሆን ግልጥ ሆኖ ይታያል ።

ይህ እንዳይሆን የመንግሥታት መሪዎች በውይይታቸው ፤ የሃይማኖት መሪዎች በጸሎታቸው እጅግ ለከበረውና በእግዚአብሔር አምሳል ለተፈጠረው ለሰው ልጅ ሕይወት ሲሉ ስለሰላሙ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ከፍተኛ ጥረት ሊያደርጉ ይገባል ።

የሰላም አምላክ እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ በተወለደበት ዕለት በመላእክትና በሰዎች አንደበት እንደተነገረ ሰላም በምድር ሰላም በባሕር ፤ ሰላም በአየር እንዲሰፍን ምእመናን ሁሉ ከልብ በመንፈስ ስሜት ሊጸልዩ ይገባል።

<u>የተወደዳችሁ ምእመናን!</u>

ነገ የምናከብረው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ልደት የደስታ የሕይወትና የነፃነት በዓል መሆኑን ተገንዝበን ነፃነት እኩልነትና ትክክለኛ ፍትሕ አጥተው ለሚቸገሩት ወገኖች ሁሉ ማሰብ ይገባናል ።

በተለይም በሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል በተነሣው ጦርነትና በድርቅ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው መጠለያ አጥተው በከፍተኛ ችግር የሚገኙትና ይህን የሰላምና የደስታ በዓል በሃይማኖታዊ ሥርዓት በየሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው ተገኝተው ለማክበር ያልቻሉ ወገኖቻችንን ልናስባቸው ይገባል ። ጦርነቱም በሰላም እንዲለወጥ ተቀዋምያን ወገኖችም ቤተ ክርስቲያናችን በተደጋጋሚ ያሳለፈችውን የሰላም ጥሪ እንዲቀበሉና ለሰላምና ለአንድነት እንዲጥሩ ችግሮች በውይይት እንዲፈቱ ቤተ ክርስቲያናችን አሁንም የሰላም ጥሪዋን ታስተላልፋለች ። በተለያየ ምክንያት ላዘኑት እግዚአብሔር መጽናናትን እንዲሰጣቸው ኀዘናቸውንም



www.ethiopianorthodox.org

ወደ ደስታ እንዲለወጥላቸው መጸለይ አስፈላጊ ነው ። በረኀብ በእርዛትና በሕማም ተጨንቀው የበዓሉን ደስታ የማያውቁም ብዙዎች ናቸው ፤ ስለዚህ የክርስቶስ በዓለ ልደት የጥቂቶች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም እንዲሆን ለተቸገሩት ሁሉ የፍቅርና የርኅራኄ ሥራ ልንጠራላቸው በሩቅም በቅርብም ያሉትን ሁሉ አቅማችን በሚፈቅደውና በዘወትር ጸሎታችን ልናስባቸው ይገባናል ። የመንፈሳዊ በዓል አከባበርም ዓላማው ይህ ነው ።

የምንኖርበት ዓለም ችግሩ አንድና ሁለት ተብሎ ተቆጥሮ የሚያበቃ አይደለም በየጊዜው የተለያዩ ችግሮች ይታያሉ ። ከእነዚህም አንዱ የሰው ልጅ ሕገ እግዚአብሔርን ባለመጠበቁ ፤ ለራሱና ለባልንጀራው ባለመጠንቀቁ በሥነ ምግባሩ ጉድለት ያመጣው የማይፈወስ ደዌ ነው ። ይህም ከጦርነቱ ከረኃቡና ከሌላው ችግር ሁሉ ጋር ተዳምሮ የዓለምን ሕዝብ ከከባድ ፍርሃትና ስጋት ላይ ጥሎት ይታያል ።

ስለዚህም እግዚአብሔር በቸርነቱ ደዌውን እንዲያርቅልን ሰውም ሕግን በመተላለፍ ከሚመጣ ደዌና መቅሠፍት ራሱን እንዲጠብቅ አዘውትሮ ማስተማር መምከርና መጸለይ ያስፈልጋል ።

በእግዚአብሔር ትእዛዝ ጸንቶ ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቆ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ፤ አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ተወስኖ መኖር ራስንና የሚቀጥለውን ትውልድ ከዚህ አደገኛና ቀሣፊ በሽታ መጠበቅ እንደሚገባ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምራ ስታስተምር ኖራለች ። አሁንም ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወቱ የተስተካከለ ወላጆቹን ተክቶ ያቆዩለትን ቅርስ ተረክቦ ሀገርን የሚያገለግል ጥሩ ጤናማ ዜጋ እንዲሆን ምእመናን ሁሉ ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቀው እንዲኖሩ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች ።

ከዚህም ጋር የጸና ሃይማኖት የቀና ምግባር ይዞ ራስ ወዳድነትንና ግላዊነትን አስወግዶ በሰላምና በፍቅር ሆኖ ሀገርንና ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን ታማኝ ሆኖ መገኘት የጥንታውያን እውነተኞች ኢትዮጵያውያን ባሕርይ ስለሆነ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያንም ሊዘነጉት አይገባም ።

እግዚአብሔር ወደዚህ ዓለም የመጣውና ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ሰው በበደሉ እንደጠፋ እንዳይቀር የሰው ፍቅር አገብሮት ነው ። እርሱ እኛን እንደ ወደደን እኛም እርስ በርሳችን እንድንፋቀር እንድንረዳዳ በቃልም በተግባርም አስተምሮናል ። ሰላምንና አንድነትንም እንድናጸና በዕለተ ልደቱ ተለያይተው የነበሩ መላእክትና ሰዎች በአንድነት ሆነው "ሰላም በምድር ፤ ለሰውም በጎ ፈቃድ" በማለት ሰላምንና አንድነትን አብስረዋል ።

ስለዚህ እኛም ዛሬ ይህን የምሥራች ደግመን ሰላም በምድር ለሰዎችም በጎ ፈቃድ ፤ በማለት ጥላቻ በዕርቅ ጦርነት በሰላም እንዲለወጥ ችግሮች በሰላማዊ ውይይት እንዲፈቱ የሚጠይቀውን የቤተ ክርስቲያናችንን መልእክት በዚህ ዐቢይ ሃይማኖታዊ በዓል ምክንያት እናስተላልፋለን ።

እግዚአብሔር ሀገራችን ኢትዮጵያን በሰላምና በአንድነት ያጽናልን ለዓለም ሁሉ ሰላምን ይስጥልን በዓሉን የሰላምና የደስታ በዓል ያድርግልን ።

አሜን!

# የሰላም አገርዋ ወዴት ነው ?

(ከብፁዕ አቡነ አብርሃም
ሊቀ ጳጳስ)

ለማንኛውም ፍጥረት መገኛና መፈጠሪያ መኖሪያ ቦታ የሌለው የለም ። ሁሉም በተወሰነ በተከለለ ቦታ ይገኛል ይፈጠራል በተወሰነ ቦታ ይኖራል በተፈለገም ጊዜ ከዝያው ቦታ ይገኛል በግል ፍላጐቱም ሆነ በአጋጣሚ ችግር ከመኖሪያው ቦታ ወጥቶ ወደ ሌላ ቦታ ቢሄድም ጠጉረ ልውጥ ላገሩ እንግዳ ለሰው ባዳ ባይተዋር በመሆኑ በአጋጣሚ ከሚያገኛቸው ሰዎች ሁሉ ከየት እንደመጣ ወዴትስ እንደሚሄድ የማንስ ወገን እንደሆነ ለምን ሥራ ምን ለማድረግ እንደመጣ ልዩ ልዩ ጥያቄ ይቀርብለታል ። ለምሳሌ ነቢዩ ዮናስ "የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነነዌ ሄዶ እንዲሰብክ በእግዚአብሔር ቃል በታዘዘ ጊዜ ከእግዚአብሔር ፊት ኰብልሎ ወደ ኢዮጴ ወርዶ ነበር ከዝያም ወደተርሴስ የምትሄድ መርከብ አግኝቶ ዋጋ በመክፈል ተሣፍሮ ነበር ። ነገር ግን ማዕበል ሞገድ ተነሥቶ መርከብዋ ልትሠጥም በተቃረበች ጊዜ ወደ ዮናስ ቀረብ ብለው ተሣፋሪዎች "ይህ ክፉ ነገር በማን ምክንያት እንዳገኘን እባክህ ንገረን ሥራህ ምንድር ነው ? ከወዴት ትመጣለህ ? አገርህስ ወዴት ነው" ወይስ ከማን ወገን ነህ በማለት የጥያቄ ናዳ እንዳወረዱበት እንመለከታለን ተጠያቂውም ለቀረበለት ጥያቄ ሁሉ በየመልኩ መመለስ ግድ ሆኖበታል ። ከመለሰ ዘንድም መተዋወቅን ይመሠርታል ። ከተዋወቀም ዘንድ የሄደበትን ሥራ ሊቀጥል ይችላል ።

እንግዲህ የፍጥረቱ ሁሉ መገኛ፥ መኖሪያ ቦታ ሲኖረው የሰላም መገኛ ቦታዋ ወዴት ነው ተብሎ ቢጠየቅ ከዚህ ቦታ ነው ብሎ የሚጠቁም ሰው ይኖርን የሚጠቁም ካለ መርተህ ወይም መሪ ሆነህ ሰላም ከአለችበት ድረስ አድርሰኝ ቢሉት ይቸገራልና የሚጠቁም የለም ማለቱ ይቀናል ምክንያቱም ሰላም የምትመላለስበት ፍለጋና ሥፍራ የለምና ። ለምሳሌ ሰሎሞን ሦስት ነገሮች ይገርሙኛል እነርሱም የንስር መንገድ በሰማይ የእባብ መንገድ በድንጋይ ላይ ፤ የመርከብ መንገድ በባሕር ላይ ናቸው ምሳ · ፴ ቁ ፲፰—፲፱ የሄዱበት ፍለጋ ምልክት የላቸውምና እንግዲህ የሰላም አገርዋ ወዴት ነው ? የተባለውን ጥያቄ ለመመለስ ሩቅ የሆነ የሕሊና ጉዞ ያስፈልጋል ግን ሩቅ አሳቢ ከቅርብ አዳሪ የሚባል አነጋገርም አለ። አዎን ተፈላጊው ነገር ከአጠገብ እያለ ርቆ በመሄድ የሚፈልግ አለ ። ይህም በዝንጋዔ (በመዘንጋት) ሊሆን ይችላል ። ለምሳሌ አንድ ሠራተኛ መጥረቢያውን በትከሻው ይዞ መጥረቢያ ፍለጋ ሄደ ይባላል ።

እንግዲህ ሜዳውን ሮጠው ፤ ሸንተረሩን አቋርጠው ፤ ጋራውን ዞረው ወንዙን ተሻግረው ቢሄዱ ሰላም የምትገኝ አይደለችም ከደመና እንደ መና ትወርዳለች እንደ ዝናምም ከወደላይ ትዘንማለች ተብላ አትጠበቅም ፤ አራቱን መዓዝነ ዓለም ዞረው ቢያስፈልጓትም ሰላም የምትገኝ አይደለችም ታዲያ በዚህ ሁሉ ዓይነት ፍለጋ ካልተገኘች በምን ትገኛለች ? ቢባል ከያንዳንዱ ሰው ቅን ሕሊናና ቅን አስተሳሰብ ከበጐ አድራጐቱ ከሰላማዊነቱ ሰላም ትገኛለች ።

እያንዳንዱ ሰው ራሱ ሰላማዊ ሆኖ መገኘት ራሱን መግዛት መጥፎ ጠባዩን ሸካራ አመሉን ማለዘብ አለበት ራሱ ሰላማዊ ሆኖ ከተገኘ አካባቢውንም ሁሉ በሰላማዊነቱ ሊሰብከው ይችላል ጥላቻ ያለባቸው ሰዎች ቢኖሩም እገሌ የሰላም ሰው ስለሆነ በጥል የተለያየነውን ሊያስማማን የተበተንነውን ሊሰበስበን ልብ ለልብ የተራራቅነውን ሊያገናኘንና ሊያቀራርበን ይችላልና ጉዳያችንን እርሱ ይይልን እያሉ ለሽምግልና ይመርጡታል እርሱም ቃሉ ተሰሚ ሽምግልናው አስማሚ በመሆኑ "መተው ነገሬን ከተተው" በሚል ምሳሌ አንተም ጎረቤትህ የጠላብህን ተው አንተም እርሱ ያልወደደልህን የጠላብህን ተው በማለት ያስማማቸዋል ወደ ሰላም ዓለም ያደርሳቸዋል በዚህ ዓይነት ሰላም በመካከላቸው ትሠፍናለች ሥር ሰዳ ቅርንጫፍዋን ትዘረጋለች የተጠጋትን የተጠለለባትን ሁሉ ታስደስታለች ሰላም ባለችበት አካባቢ ጥላቻና መቃቃር ቦታ የላቸውም አይገኙም እልም ድርግም ብለው ይጠፋሉ ። ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም "እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝ ከእኔ ተማሩ ፤ በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ የነገርኋችሁ ይህ ነው" ማቴ· ፲፩ ቁ· ፳፱ ዮሐ· ፲፮ ቁ· ፴፫ ብሎአል አዎን እርሱ ጌታችን ተበቃይነት የሌለው ለፍጥረቱ ቅን አሳቢ በፍቅር ሳቢ በመሆኑ በእኔ ሳላችሁ በእኔ ካመናችሁ እኔን ከመሰላችሁ ሰላምን ታገኛላችሁ አለን የሰላም ባለቤት የሰላም መገኛ ነውና ለሰላሙም ፍጻሜ የለውምና ኢሳ· ፱ ቁ· ፯" ሰላሜን እሰጣችኋለሁ ፤ እኔ የምሰጣችሁም ዓለም እንደሚሰጠው አይደለም ያለው የሰላሙ ምንጭ የማይደርቅ የማያልቅ ስለሆነ ነው ። "ዮሐ· ፲፬ ቁ· ፳፯" እንግዲህ ሰው ሁሉ ከመልካም ጠባዩ ከመልካም አስተሳሰቡ የተነሣ ከአካባቢው ከአዋሳኙ ጋር ያለው ግንኙነትና ማህበራዊ ኑሮው ያማረና የሠመረ ከሆነ ሰላም ከእርሱ ጋር አለች ትኖራለችም ማለት ነው" መልካም ሰው ከመልካም ልቡ መዝገብ መልካምን ያወጣል ተብሏልና ማቴ· ፲፪ ቁ ፴፭ ምንጊዜም በዚህ ዓለም የፈለጉት ሳይገኝ ያልፈለጉት ከች (ከተፍ) ይላል ።

ለምሳሌ የአማሌቅ ንጉሥ አጋግ በሳኦል እጅ ተማርኮ የሄደው ሳኦል ልጁን አጋብቶ እርሱ በግራ ቢሠለፍ አጋግን በቀኝ ሊያሰልፈው ቀኝ ክንድ እንዲሆነው ነበር ። ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ አጋግ ያላሰበውና ያልጠበቀው አስደንጋጭ ነገር ከተፍ አለበት ይህውም አጋግ በንጉሡ አጠገብ ሆኖ ሲመገብ ሳለ የጐረስኸውን (የጐረስከውን) አታኝከው ያኘከውንም አትዋጠው የሚል የሞት መልእክት ከነቢዩ ሳሙኤል መጣበት አጋግም" በውኑ ሞት እንዲህ መራራ ነውን ? ብሎ እየተንቀጠቀጠ ወደ እርሱ ወደ ሳሙኤል ሄዶ ለሞት በቅቶአል ቀዳ· ሳሙ· ፲፭ ቁ· ፰—፴፪ ።

በአኳያውም ባሁኑ ጊዜ ሀገራችን ትኩረት አድርጋ የፈለገችውና የምትፈልገው እድገትና የለሙት ገሮች ከደረሱበት ከፍተኛ ደረጃ ለመድረስ ነበር ። ነገር ግን ያልታሰበና ያልተጠበቀ ኋላ ቀር





www.ethiopianorthodox.org

## ዜና ሊቃውንት

# የመልአከ ገነት ምናሴ ዘለቀ አጭር የሕይወት ታሪክ

መልአከ ገነት ምናሴ ዘለቀ ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ.ም በላስታ አውራጃ በመቄት ወረዳ በታላቁ ደብር ገረገራ ጊዮርጊስ ከአባታቸው ከአቶ ሰፈፈ ወርቁ እና ከእናታቸው ከወ ሮ የሺ እምዐ ዘለቀ ተወለዱ እድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ ወፍጭና ማርያም ከአባ ገ/እግዚአብሔር አዳል ንባብ ዳዊትና አምስቱን አዕማደ ምሥጢር አጠናቀው ተምረዋል ። በ፲፱፻፴፪ ዓ.ም ከአቡነ ጎርጎርዮስ ማዕርገ ዲቁና ተቀብለዋል ከሩሳ ኪዳነ ምሕረት ከመሪጌታ አበባው አዳነ ከውዳሴ ማርያም ዜማ እስከ ምዕራፍ ጾመ ድጓ በሚገባ ተምረዋል ። ከሊቀ መዘምራን መንግሥቱ ውሂብም ዜማውን አጠንክረዋል ። እንዲሁም ወደ ጋይንት ሂደው ዙር አምባ ከየኔታ ታደገና ከመጋቤ መርዓዊ ከመሪጌታ ኃይሌ ዘንድ የዜማና የዝማሬ መዋሥዕት ትምህርታቸውን አስፋፍተዋል ። የቅኔ ትምህርታቸውንም ከዋድሌው መምህር ኪነ ጥበቡ ፭ኛ በቤተ ማርያም ፪ኛ በሽሜ ጊዮርጊስ ፫ኛ በወርካዬ ማርያም ተዘዋውረው የቅኔን ሙያ አጠናቀዋል ። ከሸዋው መምህር መርዓዊም ቅኔውን በሚገባ ተምረዋል ። የውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም አንድ ምታ ትርጓሜ ተምረዋል ። በትዕይንተ ጎንደር የአቋቋም ምስክር ከነበሩት ከመምህር ክፍሌ ወ/ጻድቅ የጎንደርን አቋቋም ተምረዋል እንዲሁም ሰንበትዬ ሚካኤል ከነበሩት መምህር ገ/ሚካኤል ዘንድ የክብረ በዓል የመዝሙርና የአርባ ዕት መሐትውና የቅኔ አቋቋም የወር በዓልን ቀለሞች በሚገባ አበጥረው በማወቅ በመምህርነት ተመርቀዋል ። እንዲሁም ከየኔታ ሞስ... ፍንና ከየኔታ ኢያሱ ዝማሬ ማዋ... ሥዕት ተምረው ለማስተማር በቅ... ተዋል። መልአከ ገነት ምናሴ ግን... ቦት ፲፩ ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ.ም በገረገራ ... ጊዮርጊስ ደብር መምህር ቀኜላ... ሰይፉ (አሁን አቡነ እንድርያስ)... አስተዳዳሪ በነበሩበት ጊዜ ከወ...



መልአከ ገነት ምናሴ እኒህ ናቸው

ወሰንየለሽ ጸጋው ጋር በተክሊልና በቁርባን ሥርዓተ ጋብቻን ፈጽመው ከመምህር ቀጸላ የሐዲሳትን ጉባዔ አይሄደው የትምህርተ ሀቡዓትንም ትርጓሜ አጠናቀው ወደ ቤተ ልሔም ወርደው ከመምህር አምሳሉ መርሻ ድጓውን ከነባሕሉ በሚገባ አጠናቀው ተምረው ጉባዔ ዘርግተው እንዲያስተምሩ በማኅተም የተረጋገጠ የምስክር ወረቀት ጥር ፳ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ.ም በመቀበል ተመርቀዋል ። በዚሁ ዓ.ም ከብፁዕ አቡነ ሚካኤል የቅስና ማዕረግ ተቀብለው በገረገራ ጊዮርጊስ ደብር በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን አስተምረው ለቤተ ክርስቲያን አበርክተዋል ። ከእሳቸው ዘንድም ለመማር ከመጡት መምህር ብርሃኑና አባ መዘምር የስለል ኩላ ቅዳሴን ተምረው ለማስተማር በቅተዋል ። ፲፱፻፶፯ ዓ.ም በአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ማርያም ተቀጥረው ድጓ ሲያስተምሩ ቆይተው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት መካነ ሕይወት ገ/መንፈስ ቅዱስ ደብር ከመስከረም ፯ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ.ም የማስተማር ሥራቸውን ቀጥለው ለ፰ ዓመት ያህል አስተምረዋል ።

በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም በሰላሌ አውራጃ አራተ ማርያምን ደብር እያስተዳደሩ በማስተማር ምዕመናንንም በማስተባበር በርከት ያለ ባሕር ዛፍ ከማስተከላቸውም በላይ ፳ ክፍል መንፈሳዊ ት/ቤት አሠርተው የቤ/ክርስቲያኑንም ሕንፃ በማሠራት ላይ እንዳሉ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም ወደ አ.አበባ ተመልሰው ነሐሴ ፴ ቀን ፲፱፻፷፰ የመካነ ሕይወት ገ/መንፈስ ቅዱስን ደብር እንዲያስተዳድሩ በሕዝብ ተመርጠው ጠ.ቤ. ክህነትም በማጽደቅ ተሹመው ሕንፃ ቤ. ክርስቲያኑንም በአዲስ መልክ በጥሩ ጥላን አሠርተው እስካሁንም መንፈሳዊ አገልግሎት እየተሰጠበት ይገኛል ። ምእመናኑን በማስተባበር ለመዘምራኑም ጥንግ ድርብ አሠርተው ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መልአከ ሕይወት የሚል ማዕርግ ተቀብለው ደብሩንም በማስከበር ለመጀመሪያ ጊዜ ይኸንን ስያሜ አስገኝተዋል ። ኅዳር ፴ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ.ም መልአከ ገነት ተብለው ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር አስተዳዳሪ ሁነው ተሹመዋል ። ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ.ም የደብረ ጽጌ ቅዱስ ኡራኤልን ደብር እንዲያስተዳድሩ ተሹመው ከሰበካ ጉባዔው አባላት ከልማት ኮሚቴው ጋር በመመካከር ብዙ የልማት ሥራዎችን አከናውነዋል ። የቆሻሻ መጣያ የነበረውን መካነ መቃብር የመንግሥትንም ድጋፍ በመጠየቅ በጥርብ ድንጋይ እንዲታጠር አድርገው ካህናቱንም አስተባብረው ባሕር ዛፍ ከማስተከላቸውም ሌላ ለደብሩም የገቢ ምንጭ አስገኝተዋል ። በ፳.፲፩. ፲፱፻፸፱ ደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስን ደብር ተሹመው ለአንድ ዓመት ከመንፈቅ አስተዳድረዋል።

በ፲፪.፬.፲፱፻፹፩ ዓ.ም ለ፯ ወራት ያህል እንደገና ደብረ ጽጌ ኡራኤል ደብርን ተሹመው አስተዳድረዋል ። ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መልካም ፈቃድ የቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ደብርን ተሹመው እስካሁን ድረስ በትጋት የተጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃት በመወጣት ላይ ይገኛሉ ምእመናኑንም በማስተማር ላይ ናቸው ። መልአከ ገነት ምናሴ ዘለቀ የአምስት ወንዶችና የስድስት ሴቶች በድምሩ የአስራ አንድ ልጆች አባትና የቤተሰብ ኃላፊ ናቸው ።

አዘጋጅና አቅራቢ ቀኝ ጌታ ጥዑመ ልሳን ከበደ

ነት የኢትዮጵያ ውድቀት ገጥመዋታል ። ለሰውም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል" (ማቴ ፲ ቁ. ፴፮) የተባለው አምላካዊ ትንቢት ተፈጽሞባታል ይሁን እንጂ ሁሉን ማድረግ የሚችል ምንም የሚሳነው ነገር የሌለ ልዑል እግዚአብሔር ተኩላን ከበግ ጠቦት ጋር ነብርን ከፍየል ጠቦት ጥጃን ከአንበሳ ደቦል ጋር አስማምቶ የሚያኖር በመሆኑ (ኢሳ ፲፩ ቁ. ፯) በሁሉም በኩል ስምምነትን አስገኝቶልን ሰላምን እንዲያሰፍንና የምሕረት ፊቱን ወደ ሀገራችን እንዲመልስልን በጥዋትና በማታ እንለምነዋለን ።

ስለዚህ ነቢዩ ኢሳይያስ "የጽድቅ ሥራ ሰላም የጽድቅም ፍሬ የዘላለም መታመንና ጸጥታ ይሆናል ሕዝቤም በታመነ ቤት በጸጥተኛ ማረፊያ ይቀመጣል ፴፪ ቁ. ፲፯ እና ፲፰ ያለው ትንቢታዊ ቃል በእማናዊነት ይፈጸምልን ዘንድ ጊዜያችንን የጸጥታና የሰላም ጊዜ ያድርግልን ሁከትና ሽብርን አስወግዶ ለኑሮአችን እፎይታና እረፍትን ለሀገራችንም አስተማማኝ ጸጥታን ይስጥልን ። አሜን ።

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ከመ ሉሌ መልአኩ

## ቀ/የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአዲሱ ዘመን

### ፩/ የኦቶማን ቱርኮችና ፈረንሳዮች በተከታታይ ግብጽን በጦር ኃይል ይዘው በገዙበት ወቅት የኮፕቶች

መጠነኛ ነፃነት ማግኘት ።

በቀዳማዊ ሳሌም የተመራው የቱርክ ጦር በ፩ሺ፭፻፲፯ ዓ/ም የማምለክ ዳይናስቲ ሱልጣኖችን ደምስሶ ግብጽን ያዘ ። ሆኖም የቱርክ መንግሥት ለግብጽ ግዛቱ አንድ ፓሻ (እንደራሴ) ከመሾሙ በተጨማሪ ድል የተመቱ ማምሉኮችን የየክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ አድርጎ ሾሟቸው ነበር ።

የኦቶማን ቱርኮች አገዛዝ ምንም እንኳ በእስልምና ሃይማኖት ላይ የተመሠረተ ቢሆንም መንግሥቱ በግብር አሰባሰቡ (ማስገበሩ) ተግባር በእስላሞችና በክርስቲያኖች መካከል የጐላ ልዩነት ሳያደርግ ሁሉንም ዜጎች ከሞላ ጐደል እኩል እያስገበረ ግብጽን ያስተዳድር ነበር ። የግብሩ ከፍተኛነትና የየክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ የሆኑት ማምሎኮች ጭቆና ግን አብዛኛውን ሕዝብ ከብዶ ነበር ።

በ፲፰ኛው ክፍለ ዘመን በጣም ባለጸጋ የነበረውና በመንግሥት አስተዳደርም ከፍተኛ ሥልጣን የነበረው ኢብራሂም የተባለው የኮፕት ቤተ ክርስቲያን አባል በሕይወት ዘመኑ ድሆችን በመርዳትና ቤተ ክርስቲያንን በመንከባከብ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አድርጓል ። በተለይ አንድ ብቻ ከነበረው ልጁ ዕረፍት በኋላ ከፍ ያለ ሀብቱን ለግብጽ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት በማውረስ ፡ ሀገሪቱን ይገዛ ከነበረው ከቱርክ ሱልጣን አስፈቅዶ ያረጁና የፈራረሱትን ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት በገንዘቡ በማሳደስና በማሠራት ፡ እንዲሁም ቁም ጸሐፊዎችን ቀጥሮ የተለያዩ የጥንትና በየጊዜው የተዘጋጁ መንፈሳዊ ነክ መጻሕፍትን እያስገለበጠ በማደል ያደረገው የበጎ አድራጐት ልገሣ ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን መጠናከርና ለመንፈሳዊው ትም



www.ethiopianorthodox.org

ሀርት መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋ ጽኦ አድርጓል ። እሱም ፈረንሳዮች ግብጽን ከመያዛቸው ቀድም ብሎ በ፩ሺ፰፻፺፯ ዓ/ም ዐረፈ ።

በናፖሊዮን ዘመነ መንግሥት ግብጽ በፈረንሳይ ተይዛ ከተገኘች በት ወቅትና (፩ሺ፯፻፺፰ እስከ ፩ሺ፰፻፩ ቀደም ሲል የመስቀል ጦርነት ከተካሄደበት ጊዜ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ የግብጽ በሮች ለምእራባውያን ዲሞክራሲ የፖለቲካ እስተሳሰብ ክፍት ሆኑ።

ምንም እንኳ በእምነት (ክርስቲያንነት) ወገኖቻቸው የሆኑት የፈረንሳይ ገዥዎች ለኮፕቶች የተለየ አስተያየት ባያደርጉላቸውም ቀድሞ ከዐረቦች ይደርስባቸው ከነበረው ከባድ ጭቆና ገላገላቸው። በዚህ አኳኋን በእስላሞችና በኮፕቶች መካከል የነበረው የልዩነት ግድግዳ በኦቶማን ቱርኮችና በፈረንሳዮች አገዛዝ ወቅት በመጠኑ መፈራረስ ጀመረ ።

ቀደም ሲል ፣ እንዲሁም በናፖሊዮን የቅኝ ግዛት ዘመንና በተለይም በ19ኛውና በ20ኛው ክፍለ ዘመን የተለያዩ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ወደ ግብጽ ገብተው በእስላሞች ተጽእኖ ለዘመናት ብዙ ችግርና መከራ የደረሰባትን የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በመርዳት ጌታ ሐዋርያትን “እንግዲህ ሄዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓችው ።...” (ማቴ.፳፰ — ፳0) ብሎ ባዘዘው መሠረት ክርስትናን ያልተቀበሉትን ሰዎች በማስተማር ፈንታ በየሀገሮቻቸው አምባሳደሮች አማካይነት የቱርክ ሱልጣኖችንና የግብጽ ፓሻዎችን እያግባቡ ለኮፕት ምእመናንም በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከፍተኛ ትምህርት እንድትማሩ እናደርጋለን ፣ የተሻለ ሥራም እንሰጣችኋለን ወዘተ... እያሉ በመደለል ኢክርስቲያናዊ በሆነ መንገድ ጥቂት ኮፕቶችን ወደ እምነታቸው መልሰዋል ። ይህንኑ ሕገ ወጥ ድርጊት የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጥብቅ ተቃውመውታል ። ምእመናንም በቀጥተኛው የተዋሕዶ እምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ በትጋት አስተምረዋል። ለምሳሌ የእስክንድርያው ፓትርያርክ አቡነ ጴጥሮስ ሰባተኛ (፩ሺ፰፻፲ — ፩ሺ፰፻፶፫) ካህናትን በማስከተል በመላ ግብጽ እየተዘዋወሩ ኮፕቶች የካቶሊክና የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ከሚያስተምሩት የተሳሳተ ትምህርት ርቀው በቀጥተኛ የተዋሕዶ እምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ አድርገዋል ። ለእምነታቸው መመሪያና ማጠናከሪያ የሚሆኑ የመሠረተ ሃይማኖት ትምህርትም አዘጋጅተው አበርክተዋል ።

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፫ የዞረ)

ኖት ምክንያት ይጣላሉ ተጣልተውም አይቀሩ የጥላቻ ውጤት መለያየት ስለሆነ አባት ከልጅ እንዲሁም ልጅ ከአባት ስለሚለይ ነው ሰላምን ያመጣሁ አይምሰላችሁ ያለው ። የዚህም ዓይነት ሥራ ከዚህ በፊት ታይቷል ለምሳሌ አንድ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዕውሩን ዓይን አበራ ፣ በዚህ ጊዜ ፈሪሳውያን በሰንበት ቀን የዕውሩን ዓይን አብርቷልና የእግዚአብሔር ወገን ካልሆነ እንዴት አድርጐ ዕውሩን ሊያድን ይችላል በማለት ከሁለት እንደ ተከፈሉና እንደ ተለያዩ በዮሐንስ ወንጌል በም· ፱—፲፯ በሰፊው ተጽፎ ይገኛል ጌታም መለያየትን እንጂ ሰላምን አላመጣሁም ለማለት የቻለው ሰው ሁሉ በሃይማኖት ምክንያት እንደሚለያይ ሲያመለክት ነው እንጂ ሌላ አይደለም።

የ፫ኛውም ጥያቄ ፊተኛው ኋለኛው ብሎ ገልጦ ተናግሮታል ይኸውም ፊተኛው ያለው ሕገ ኦሪት ኋለኛው ያለው ደግሞ ሕገ ወንጌል ነው ። ኦሪት ይህንን ሥሩ ይህንን ግን አትሥሩ እያለ የእግዚአብሔርን ሕግና ሕልውና ቢያሳውቅም ከፍዳ ከኃጢአት ነፃ አያደርግም ነበር እንዲያውም ዓይን ያጠፋው ዓይኑ ይጥፋ ጥርስን የሰበረ ጥርሱ ይሰበር የሚል ሕግ ስለነበረ ነቀፋ ነበረበት ሕገ ወንጌል ግን ከዚህ ሁሉ የተለየ ሕገ ጽድቅ ከመሆኑም ሌላ የሰደበህን መርቀው ቀኝ ፊትህን ለመታህ ግራ ፊትህን አዙርለት የሚል ነው ።

ስለዚህ አሁን ግን በሚሻል ተስፋ ቃል በተመሠረተ በሚሻል ኪዳን ደግሞ መካከለኛ እንደሚሆን በዚያ ልክ እጅግ አገልግሎት አግኝቷል ካለ በኋላ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለኦሪትና ስለ ወንጌል በማበላለጥ ሲገልጽ ፊተኛው ኪዳን ነቀፋ ባይኖረው ለሁለተኛው ኪዳን ሥፍራ ባላስፈለገውም ነበር ብሏ ል ።

ሐዋርያው በዚህ ሳይወሰን ከብሉይ ኪዳን በኋላ ሐዲስ ኪዳን እንደሚሠራም በማስመልከት እነሆ ከእሥራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ሲል ጨምሮ ገልጧል ይህም ማለት በኋለኛው ዘመን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሕገ ወንጌልን ማስተማሩን ሲያመለክት ነው ።

ክንፈርግብ ማርቆስ



# በሰሜን ሸዋ የምትገኘው የግፍት ማርያም ታሪክ በአጭሩ

ይህቺ ቤተ ክርስቲያን የተተከለችው በአፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ሲሆን በሰሜን ሸዋ አስተዳደር በሞላሌ አውራጃ ከዚህ ከአዲስ አበባ ወደዚያው ስንሄድ መዘዞ የተባለችውን አነስተኛ ከተማ አለፍ ብለን ጥፍጥፍ ድንጋይ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ስንደርስ ቤተ ክርስቲያኗ ዙሪያዋን ኮረብታም በሆነ ቦታ ላይ በአራቱም ማዕዘን የምትታይ ፣ እንደ መሶበ ወርቅ ክብ ሆና የተሠራችና ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የመስቀል ቅርፅ ያለባት በጠቅላላ የቦታዋ አቀማመጥ እንደግሸን ማርያም ነች ብንል ማጋነን አይሆንም ። ከዚህ በማያያዝ ።

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ገቢረ ተአምር በቅደም ተከተል እንገልጻለን ።

፩ኛ) ጠላት አገራችንን ከመውረሩ አስቀድሞ አንድ ሌባ ጽላቷን ለመስረቅ ወደዚችው ቤተ ክርስቲያን ይገባና ከመንበሯ ላይ ታቦቷን አንሥቶ ለመሄድ ሞክሮ መንቀሳቀስ ተስኖት ከዚያው ከመንበሩ አጠገብ እንደ ድንጋይ በድን ሆኖ ተገኝቷል ።

፪ኛ) በ፲፱፻፳፱ ዓ·ም ጣሊያኖች ወደዚች ቤተ ክርስቲያን ለመግባት የተደጋመመ ሙከራ አድረገው ሳይሳካላቸው በመቅረቱ በርቀት ጋራ ጋራውን ዙሪያውን እየተመላለሱ ከአዩ በኋላ ይህችስ ኃይለኛ ታቦት ነች ብለው በመጡበት እግራቸው አፍረው ተመልሰዋል ።

፫ኛ) በ፲፱፻፴፩ ዓ/ም በዚሁ በቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ የሚኖሩ አዛውንት እንዲህ በማለት ገልጸዋል ። ይህን የምታዩትን ልጇን አሥራተ እስግዶ የተባለውን ክርስትና ለማስነሣት ያዘጋጀነውን ጠብል ጠዲቅ አሽከሜ ሄጄ ከቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ስንደርስ እንስራው ድንገት ሳያስበው ከስውየው ትከሻ ላይ ያመልጠውና እንደ ቆመ ይለቀዋል ነገር ግን እንሥራው አልተሰበረም እያስገርመንም እንስራው ሳይሰበር ጠላውም ሳይደፋ መቅረቱ ነው ብለዋል ።

፬ኛ በ፲፱፻፵ ዓ/ም አሁንም በዚሁ በቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ የሚኖሩ አንድ ካህን በስተምሥራቅ በኩል ኩዎሉ የተባለ እሾህ ያለበትን እርጥብ እንጨት ሲለበልቡ በድንገት ከየት መጣ የማይባል አውሎ ነፋስ ተነሥቶ በቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ የሚገኙት መቃብር ቤቶች በእሳቱ ተያይዘው ይቃጠላሉ ። ከዚያም ይኸው እሳት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ከመዛመቱ በፊት ለጊዜው የተገኘውን አንድ እንስራ ውሃ በመሰላል ቤተ ክርስቲያኑ ላይ ያወጣሉ በጉልላቱ ላይ ያሉ ንቦችም ወጥተው ቅጥር ግቢውን ወረውታል እሳቱ ወደ ዓፀድ ይዛመትና ከዚያም የተቀጣጠለው እሳት በ፫ አቅጣጫ ከቤተ ክርስቲያኑ የሣር ክዳኑ ላይ ሲያርፍ እንስራው ሙሉውን ውሀ እንደያዘ ለማጥፋት እንኳ ሳይሞክር ከመቅጽበት ከሰውየው እጅ ያምልጥና ከመሬት ወርዶ ቂጭ ከማለት በስተቀር እንስራው አልተሰበረም ውሃውም አልፈሰሰም ።



ጥንታዊቷ የግፍት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይህች ናት

ወዲያው የእሳቱም ነበልባል የሣር ክዳኑን ለብለብ እንኳ ሳያደርገው በቀስተ ደመና መልክ ተለውጦ በጉልላቱ ላይ አልፎ ሲሄድ ንቦችም ወዲያው ወደ ጉላልቱ ተመልሰው ገቡ ። በጊዜው የነበሩና ለዕርዳታውም የደረሱ ካህናትና ምዕመናን ይህንን አስደናቂ የሆነ ተአምር ስለአሳየሽን ዕፁብ ድንቅ እያልን እናመሰግንሻለን ፣ እናወድስሻለን በማለት ከተማፀኑን በኋላ ብዙዎቻችን ወደየቤታችን ስንመለስ አንዳንዶቹ ግን በዚያው የሙጥኝ ብለው ቀርተ



www.ethiopianorthodox.org

ዋል ።

፭ኛ) በዓለ ንግሷን ለማክበር ጽላቷን የሚያነሣው ወይም የሚቀድሰው ቄስም ሆነ ዲያቆን ሙሉ በሙሉ በንጽሕናው መተማመን ይኖርበታል ። ይህ ሳይሟላ ከቀረ ግን በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ሁኔታዎች መከሠታቸውን እዚያው በቅርቡ የሚገኙት ካህናትና ምዕመናን ስለሚያውቁት ይህ ነው ብለን በዝርዝር ለመግለጽ ምናልባት አንዳንዶችን እዚያው በቅርቡ የማገኙትን ቅር የሚያሰኛቸው በመሆኑ ከመጻፍ ተቆጥበናል ። በበዓለ ንግሡም ዕለት ቅድስት ድንግል ማርያም የምታሳየውን ድንቅ ተአምር ሕዝበ ክርስቲያኑ ከተመለከተ በኋላ ካህናቱ በዝማሬ ወንዱ በሆታ ሴቱ በጭብጨባና በዕልልታ አክብረው በዓለ ንግሡ በታላቅ ክብር ይፈጸማል።

፮ኛ) አሁን በቅርቡ አዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ አንድ ግለሰብ እንደተናገሩት እኔ በግፍት ቤተ ክርስቲያን የምገኝ ቅድስት ድንግል ማርያም ነኝ መጋረጃ ገዝተሽ ላኪልኝ ስትል በሕልሜ አሳየችኝ ታዲያ ምን ማድረግ ይሻለኛል? ይኸ ግፍት የሚባል አገር ወዴት እንደሆነ እኔ አላውቀውም በማለት አንዱ በአንዱ ከተጠያየቁ በኋላ በመጨረሻ ስለደረሱበት ፤ ቀይ መጋረጃ በ፸፭ ብር ገዝተው ስለላኩ በሴቶች መቋሚያ በኩል ተጋርዶ ይታያል ።

፯ኛ) አሁንም በዚሁ በአዲስ አበባ ውስጥ የሚኖሩ አንድ ግለሰብ ሴት ችግር ገጥሟቸው በተለያዩ ቦታዎች እየሄዱ ሥዕለት ቢሳሉም ለጊዜው በፈለጉት ሰዓት ሊፈጸምላቸው ባለመቻሉ ፤ ግራ ተጋብተው በመበሳጨት ላይ እንዳሉ የዚችው የግፍት ማርያም ተወላጅ የሆኑ ለእኔ አገር ታቦት ሳትጠራጠሪ ብትሳይ ወዲያው ይደርስልሻል ስለአሏቸው እንደተባለውም ሥዕለታቸው ሊፈጸምላቸው በመቻሉ እሳቸውም እንደ አጋጣሚ የተሳሉት መጋረጃ በመሆኑ ተጋርዶ ይገኛል ።

አሁን ይህ ዝነኛና ባለታሪክ የሆነው የሣር ክዳን ቤተ ክርስቲያን በአካባቢውና በአዲስ አበባ ከሚገኙ ምዕመናን ገንዘብ ተሰብስቦ በቆርቆሮ ስለተከደነ ከቀድሞው በበለጠ ሁኔታ ላይ ሲሆን ለዚህችም ቤተ ክርስቲያን ብቁ የሆነ አገልግሎት የሚያበረክቱ መዘምራን ፤ ቀሳውስትና ዲያቆናት ይገኙበታል ።

እነዚህም ካህናት ለመንፈሳዊ አገልግሎት ያላቸው ንቃትና ትጋት ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ ፍቅረ ቢጽ ያደረባቸውና የእንግዳ አቀባበል ሥነ ሥርዓታቸውም ከፍተኛ በመሆኑ እጅግ በጣም ሊመሰገኑ የሚገባቸው ናቸው ።

፰ኛ እንዲሁም መታለፍ የሌለበት ፡ በዚሁ በአዲስ አበባ በከፍተኛ ፲፩ ቀበሌ ፲፪ በቤት ቁጥር ፰፻፸፭ የሚኖሩ ስማቸው ሊጠቀስ ያልፈለጉ ግለሰብ በአለቻቸው አቅምና ችሎታ የእመቤታችንን የቅድስት ማርያምን በረከት ለመቀበል ሲሉ ከሚአገኟት አነስተኛ ደመወዛቸው ላይ ትንሽ ትንሽ እያጠራቀሙ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ከጧፍ ዕጣንና ዘቢብ ጀምሮ እስከማኸ ከመጻሕፍትም ለቤተ ክርስቲያኑ ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጣሉ ከተባሉት ውስጥ አምስቱ ጸዋትወዜማ መጽሐፈ ግጻዌ ፤ ዚቅና ተአምረ ማርያም የመሳሰሉት ሲሆኑ ፤ ከአልባሳት የ5 ሰሞነኞች መቀደሻ ልብሰተክህኖ ብዙ የተለያዩ ሥዕሎችና ከነዚሁም ውስጥ በተለይ ሁለቱ ሥዕለ አድኅኖ (ምስለ ፍቁር ወልዳ) ውድ ዋጋ ያላቸው በፊርጥና በወርቅ ዘቦ በአቶ አሥራት ወልደ መድኅን የተሳሉ ናቸው እኚህ ግለሰብ ለአስተርእዮ ማርያምና ለግንቦት ማርያም በዓመት ሁለት ጊዜ በዓለ ንግሷን ለማክበር ወደዚሁ አገር በሚሄዱበት ሰዓት ታሪኳን የሰሙ መዘምራንና ምእመናንም አብረዋቸው በመሄድ ክብረ በዓሉን ከአከበሩ በኋላ፤ አብረዋቸው ይመለሳሉ ።

አሁን በቅርቡ የዚህ ታሪክ አዘጋጅና አቅራቢ የሆንኩት ለደብረ ምጥማቅ ክብረ በዓል በማክበር ሄጄ እንዳየሁትና እንደተመለከትኩት ፤ ሁሉ ከዚህ ከአዲስ አበባና ከተለያዩ ቦታዎች ሥዕለት እየተሣሉ የደረሰላቸው ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ እየተደሰቱና በዓሉንም በታላቅ ክብር እያከበሩ ሲመልሱ ተመልክቻለሁ ።

እኔም ሆንኩ ከእኔም ጋር በዓሉን ለማክበር አብረውኝ የሄዱት ሁሉ የቅድስት ድንግል ማርያምን ገቢረ ተአምር በማድነቅ ያድከዋ ወርእኩ ሥነ ሕንፄሃ ለደብረ ማርያም ገነት ይእቲ ነቅዓ ገነት አዘቅት ማየ ሕይወት ማኅደር ለንጹሐን በማለት አድናቆታችንን ገልጸን ተመልሰናል ።

ከዚህም በበለጠ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ከቦታው ድረስ በመሄድ የዚህችን ቤተ ክርስቲያን ታሪክና ገድል እንደሚረዳልን እንጠራጠርም በተጨማሪም ላሳስብ የምውደው ማንኛውም ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ ይህችን የተቀደሰች ቦታና ቤተ ክርስቲያን እየሄደ ቢጎበኝ በመንፈሳዊ ደስታ ተመልቶ የሚመለስ መሆኑን ነው ።

የዜናው አቅራቢዎች
ቀኝ ጌታ ጥዑመ ልሳን ከበደ
ተስፋዬ ሞገሴ

# በጥምቀት ሁለተኛ ልደት

ማንኛውም ሰው ሁለት ልደት እንደሚያስፈልገው የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል ። ነገር ግን አንድ ሰው ሁለት ጊዜ መወለድ ያስፈልገዋል ብለን ቃሉን ብቻ ብናስቀምጠው ምን ለማለት እንደፈለግን ወይም ምን ማለታችን እንደሆነ ስሚው ለመረዳት ያስቸግረዋል ፤ ስለሆነም ሁለት ዓይነት ልደት ማለት አንዱ ከእናትና ከአባት አብራክ ተከፍሎ መወለድ ማለት መሆኑንና ይህም የሥጋ ልደት ተብሎ እንደሚጠራ ማስረዳት ፡ ሁለተኛው ልደት የምንለው ዳግም ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ መወለድና የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ማለት ነው ብለን ማስተማር ያስፈልገናል ።

ሌላው ዳግም ወይም ሁለተኛ ልደት የምንለው የሙታን ትንሣኤ ነው ፡ የሙታን ትንሣኤ ዳግም ልደት ይባላል ። ይህም ደግሞ ልደት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚገኘውን የአዲስ መንፈስ ሁኔታ የሚያመለክት ነው ። ወደርእሱ ትምህርታችን እንመለስና ማንኛውም ሰው የእግዚአብሔር ቃል ከተፃሐደው ከውኃ ተጠምቆ ዳግም ልደት ማግኘት ያስፈልገዋል የሚለውን የእምነት መሠረት ከሁሉ በፊት አምኖ መቀበልና መፈጸም እንደሚገባው ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምረበት ዘመን ከአይሁድ ሊቃውንት መካከል አንዱና ዋንኛው የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል ምሁረ ኦሪት ሰው ነበረ ። ይህ ሰው ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሚያውቁና ከመራቀቁም በላይ በፍልስፍና ትምህርት ተመራማሪ እንደነበር ይነገርለታል ። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚመለከቱ ቃለ ትንቢቶች እንደሌሎቹ ሊቃውንት በቃል ብቻ ሳይሆን በጥቅትና በጥልቀት ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚመረምርና የሚያመሠጥር ሊቅ ነበር ከዚህም የተነሣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካለበት ሥፍራ ሌሊት እየሄደ ይማርና ይመራመር ነበር ።

ኒቆዲሞስ ከዕለታት አንድ ቀን ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግር ተቀምጦ ሲማር ከቆየ በኋላ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ? ጣዕመ ቃል ሰምቶ ተአምራዊ ሥራዎቹንም አይቶ መምህር ሆይ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን አለው ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከኒቆዲሞስ የተሠነዘረውን የእምነት ቃል ተቀብሎዝም ለማለት ስላልፈለገ "እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም" የሚል አስቸጋሪ ኃይለ ቃል አፈቱ ደቀነበት ፡ ኒቆዲሞስ ይህ ዱብ ዕዳ ሆኖ የታየውን ኃይለ ቃል በአንክሮትና በተደሞ ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ሲያስብ ቆይቶ "ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ዳግመኛ ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? ሲል ጌታችንን ጠየቀ ። እነሆ ኒቆዲሞስ እንኳ የተማረና የተመራመረ ምሁረ ኦሪት ሲሆን የዳግም መወለድ ምሥጢር ተሠውሮበትና መረዳት አቅቶት ጥያቄ ሲያቀርብ ያልተመራመረና ያልተማረማ ስለ ዳግም ልደት ምሥጢር ቢነግሩት ምን ዓይነት ጥያቄ ያቀርብ ይሆን?

በመሠረቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት እንደሚያጠምቅ ኒቆዲሞስ ከመጻሕፍትም ከመምህራንም ሳይሰማ አልቀረም ይሆናል ፡ እያወቀው ሳለ ግን ከልቡ ስለተሠወረበት ሁለተኛ የሥጋ ልደት ያለ መስሎት ከላይ እንደሰማነው በአድናቆት ጥያቄውን ለጌታችን ያቀርባል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን "እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ሲል የሁለተኛን ልደት ትርጉም (ምንነት) አብራርቶ ነግሮታል ።

ሆኖም ኒቆዲሞስ አሁንም ነገሩ ሊገባውና ሊረዳው ስላልቻለ ይህ እንዴት ይሆናል? የሚል ጥያቄውን መላልሶ በማቅረቡ አንተ የእሥራኤል መሪ ስትሆን ይህን አታውቅም?እውነት እውነት እልሃለሁ የምናውቀውን እንናገራለን፡ ያየነውንም እንመሠክራለን፡ ምስክርነታችንም አትቀበሉትም ስለምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ ስለሰማያዊ ነገር ብንነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ? ሲል የልቡን አለማስተዋል በማድነቅ የቅሬታ ንግግር መልሶለታል ። (ዮሐ.፫ ፡ ፩—፲፪)

ወንጌላዊው ዮሐንስ ስለ ዳግም ልደት ወይም በጥምቀት ሁለተኛ ልደት እንዳለ በወንጌልም በመልእክታቱም በሰፊው ጽፎአል ለምሳሌ " ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእ



www.ethiopianorthodox.org

ግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም፣ ወይም ከሥጋ ፈቃድ ፡ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም” ይላል “ከእግዚአብሔር መወለድ ማለትም ቃሉ በተዋሐደው በውኃ መጠመቅ ማለት ነው።

እንዳንድ ሰዎች በውኃ መጠመቅ ማለት መንጻትን ያመለክታል ይላሉ ፤ ይህም ማለት አንድ ሰው ሰውነቱ ሲያድፍ በውኃ ታጥቦ ከእድፉ እንደሚነጻ ማለት ነው ፣ ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ አባባል ትልቅ ስሕተት መሆኑን (እንደሆነ) እንመለከታለን ፡ እንዲያውም ጥምቀት በመንጻት ደረጃ የተሠራ (የሚሠራ) ቢሆን ኖሮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ባላለም ነበርና አባባሉ የአምላክን ሥራ መቃወም ነው እንላለን ። ጥቂቶቹ ደግሞ ጥምቀት ማለት በቃሉ ማመንን የሚያመለክት ነው ይላሉ ፡ ይህም ሠርቶ እንድንሠራ ያሳየንን አምላክ ወልደ አምላክ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ ትምህርቱን ተአምራቱን ማጣመም ነው ። ምክንያቱም እንደኛ ወደ ዮርዳኖስ ሄዶ በእገልጋዩ በመጥምቀ መለኮት ዮሐንስ እጅ መጠመቅ ባላስፈለገውም ነበር ፤ ሁለተኛም በውኃ መጠመቅ ባይጠቅም ኖሮ ሐዋርያት አረማውያንን አስተምረው ያሳመኑአቸው ሁሉ በመጨረሻ ማሠሪያው ጥምቀት መሆኑን ስለሚያውቁ ያጠምቁአቸው እንደነበረ የሐዋርያት ሥራ በየምዕራፉ ይነግረናል ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ዳግም ልደት ወይም በጥምቀት ሁለት ጊዜ ልደት እንዳለ ሲያስረዳ “ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ እንደምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረገነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም” ሲል ለደቀ መዝሙሩ ለቲቶ በጻፈለት መልእክቱ አብራርቶ ጽፎአል ።

ነገር ግን በጥምቀት ያገኘነው ዳግም ልደት መለኪያው የጽድቅን ሥራ ሠርተን ስንገኝ ብቻ ነው ፣ ወንጌላዊው ዮሐንስ በአንደኛው መልእክቱ ጻድቅ እንደሆነ ካወቃችሁ ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ከእርሱ እንደተወለደ እወቁ” ሲል አስገንዝበዋል” እንዲሁም ጻድቅ ሰው ማለት ከመንፈስ ቅዱስና ከውኃ የተወለደ ኃጢአትን አይሠራም ይላል ይህም አባባል ሰው ሆኖ ኃጢአት አይሠራም ዕንጨት ሆኖ አይጨስም ለማለት ባይቻልም ጻድቅ ሰው አንዳንድ ጊዜ ቢሳሳት እንኳ ኃጢአትን እንደማያዘወትር ወይም ለኃጢአት እሺ በጄ ብሎ ከኃጢአት ጋር ተቆራኝቶ እንደማይኖር የታመነ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው ፣ ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ ሲናገር ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአት አያደርግም ዘሩ በእርሱ ይኖራልና ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም ብሎአል ። (፩ኛ ዮሐ ፫ ፣ ፱) እልፍ ብሎም ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን እንዳያደርግ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወለደው ራሱን እንዲጠብቅ ክፉውም እንዳይነካው እናውቃለን ይላል ። ፩ኛ·ዮሐ ፭ ፡ ፲፰)

በጥምቀት ሁለተኛ ልደትን ያገኘ ዘወትር ፍቅርን ያሳያል ፡ ልዩነት ፡ ጥል ፡ ክርክር ፡ ሐሜት ፡ ምቀኝነት አይወድም ፤ አመለካከቱ ሁሉ በእኩልነት ነው ፤ ቢያኅ ቀይሙት አይቀየምም ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያዘዘውን ሁሉ ለመፈጸም ይተጋል ይነቃል እንጂ ፤ ስለእምነቱ በጸሎት ይተጋል ፤ ቃሉን በመመስከር ይነቃል ፤ እንደበቱን ከክፉ ነገር ይጠብቃል ፡ ችግር ፡ መከራ ፡ ስደት ቢደርስበትም በትዕግሥት ያሳልፈዋል ። (፩ኛ· ዮሐ ፬ ፡ ፯) ዓለምና ምኞቱ ሁሉ ኃላፊና ጠፊ መሆኑን ስለሚያውቅ ከዓለም የሆነውን ሁሉ በአሸናፊነት ይወጣዋል። የአሸናፊነት ኃይል የሚጐናጸፈውም በትዕግሥት ፡ በፍቅር ፡ በትሕትና በማሳለፍ ፡ ሰምቶ እንዳልሰማ ፡ አይቶ እንዳላየ ሆኖ ከላይ የተጠቀሱትን የጽድቅ ሥራዎች ይከታተላል ይፈጽማል ፡ በአጠቃላይ ትኩረቱ ሁሉ ወደ ፍጹምነት ደረጃ ለመድረስ ያጋድላል ማለት ነው ፩ኛ· ዮሐ ፭ ፡ ፬ ።)

ስለዚህ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀን ባገኘነው ዳግም ልደት መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ እንችል ዘንድ ከኃጢአት ርቀን ፣ ንጽሕናን ጠብቀን መኖር ይገባናል ፤ በጥምቀት ያገኘነው የእግዚአብሔር ልጅነት በመንግሥተ ሰማያት በሕይወት መዝገብ ያስመዘገበን ስለሆነ ለዘለዓለም በሕይወት ከመንኖርበት ከመንግሥተ ሰማያት እንዳንወጣ ክርስቲያናዊ ኑሮዋችንን በተቀደሰ ጎዳና እንዲመራ ማድረግ አለብን ። ለሌሎችም መልካም አርአያ ሆነን ለመገኘት እንችል ዘንድ በኃይሉና በቅዱስ መንፈሱ እንዲረዳን ፣ በእምነትና በቅድስና ሁነን በጸሎት ፈጣሪያችንን ዘወትር እንለምነው ።

ሊቀ ትጉሃን ገብረ ክርስቶስ
ኃ/ማርያም

# አሰደናቂ ተአምር

ተአምር ማለት አንዱን ፍጥረት ከነበረው የተፈጥሮ መልኩ ወደ ሌላው መልክ መለወጥ ነው። የዚህ ዓይነት ሁሉ ተአምር ይባላል ይኸውም ነጭ የነበረውን ማጥቆር መራራ የነበረውንም ማጣፈጥ ጥሩ ውኃ የነበረውንም ወደ ወይን ጠጅ መለወጥና ይህንን የመሰለ ሁሉ ተአምር በመባል ይጠራል ።

ለምሳሌ አንድ ጥቁር ሰው ሰውነቱ በለምፅ ነጭ ሁኖ የነበረውን ለምፁን አንጽቶ ወደ ቀድሞ መልኩ መለወጥ ፤ ማቴ ፰—፫ መራረ የነበረውንም ውኃ በእግዚአብሔር ከሃሊነትና በጸሎት ኃይል ማጣፈጥ ታላቅና አሰደናቂ ተአምር ነው አንድ ጊዜ ነቢዩ ኤልሳዕ መምህሩ ኤልያስን ሸኝቶ ሲመለስ ሠማርያ ወደ ተባለው ቦታ ደረሰና ወላድ ብትጠጣው የሚያመክን መካን ብትጠጣው ሆድዋን በጥብጦ የሚገድል ውኃ ነበረ ታድያ ነቢዩ ኤልሳዕ ከመራራው ውኃ ምንጭ አዲስ ሸክላ አድርጎ ጨው ጨምሮ ቢጸልይበት ያ ሲጠጡት የሚምረውና ምላስን የሚጐመዝዘው ጣፋጭ እንደሆነ በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ፪—፳፩ ተገልጾ እናገኛዋለን።

ከእነ እልሳዕ በፊት የነበረው ሊቀ ነቢያት ሙሴም ውኃውን ወደ ደም እንደለወጠው በዘጸአት ፯·፳፩ ተጽፎ ይገኛል ። ይህ ሁሉ ተአምር ተብሎ ይጠራ እንጂ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገው ተአምርና እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ተአምራቶች የተለያዩ ናቸው ምክንያቱም ሌሎቹ ምክንያት አላቸው ሙሴ ውኃውን ወደ ደም የለውጠው በያዘው ብትር በመምታት ነው ኤልሳዕም መራራውን ውኃ ሊያጣፍጠው የቻለው በጨውና በአዲስ ሸክላ አድርጎ በመጸለይ ሲሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ የለወጠው አንድም ምክንያት አልነበረውም ።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተአምር የተለየ ነው የምንለውም ስለዚህ ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን ያስተምርበት በነበረበት ጊዜ በገሊላ አውራጃ ልዩ ስምዋ ቃና በመባል በታወቀችው መንደር ሠርግ ተደረገ ሠርግ ያደረገውም ሰው በድግነቱ የታወቀ ስለነበረ የደስታው ተካፋዮች ሁነው ከሠርጉ እንዲገኙለት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፲፪ ሐዋርያትን ጠራቸው ።

እመቤታችን ጌታችንና ደቀ መዛሙርቱም ሁሉ ጥሪውን አክብረው ከሠርጉ ተገኙ ይሁን እንጂ ሙሽራው የጠራቸው ሰዎች እጅግ ብዙ ስለነበሩ ገና ከተጠሩት ሰዎች ግማሾቹ እንኳን ሳይመጡ በመካከል ያ ተዘጋጅቶ የነበረው የወይን ጠጅ አለቀ ጋኖቹ ሁሉ ባዶ ሆኑ በዚህ ጊዜ ሠርግ ያደረጉ ሰዎች ከወንድም ሆነ ከሴት ከባዕድ ሆነ ከዘመድ መጠጡ አልቆዋል ብሎ የነገራት ሳይኖር ማለቁን አውቃ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በራስዋ ሐሳብ በራስዋ ርኅራኄ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀረብ ብላ የወይን ጠጅ እኮ አለቀ ይህ የታደመው ሕዝብ ምን ሊጠጣ ነው አንድም ሰው በእጁ ብርጭቆ የያዘ የለም ሰዎቹም በኃፍረት ላይ ሊወድቁ ነው ስትለው የእናት ልመና ፊትን የማያስመልስ አንገትን የማያስቀልስ ነውና (ምንት ብየ ምስሌኪ ኦብእሲቶ) ታዲያ ካንቺ ጋር ምን አለኝ የሚል መልስ ሲመልስላት በከሃሊነቱ ቸርነቱን እንደሚገልጽ ሙሉ በሙሉ ታምነው ስለነበረች ወደ አሳላፊዎች ሂዳ በሉ ነግሬላችሁአለሁና ያዘዛችሁን አድርጉ አለቻቸው እነሱም ምን እንደሚያዛቸው ወደ እሱ ሲቀርቡ ጋኖቹን ጥሩ ውኃ ሙሉዋቸው ሲል አዘዛቸው እነሱም ባዘዟቸው መሠረት ውኃውን እየቀዱ ጋኖቹን ሞሏቸው ።

ከዚህ በኋላ በሉ ቅዱና አስቀድማችሁ ለሊቀ ምርፋቁ (ለአሳዳሪው) ስጡት አላቸው የምርፋቁ አለቃ የሰጡትን ቢቀምሰው ከዚያ በፊት ቀምሶት የማያውቀው እጅግ መልካም የሆነ የወይን ጠጅ ሆኖ ስላገኘው እጅግ ተደነቀ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ የለወጠው ጌታችን መሆኑን አላወቀም ነበርና ሠርግ ያደረገውን ሰው ጠርቶ ይህንን የመሰለውን የወይን ጠጅ ሸሽገህ ቅራሪውን ስታጠጣ የዋልከው ይህ ለማን እንዲሆን አስብህ ነው? አለው

በዚህ ጊዜ አሰላፊዎቹ ተጠርተው ቢጠየቁ እኛ ውኃውን ሙሉ አለን በታዘዝነውም መሠረት ውኃውን ሞላን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አለን እንጂ እኛ የምናውቀው ነገር የለንም ብለው ምስክርነታቸውን ሲገልጹ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥሩውን



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ዕረፍት

## የመልአከ ብርሃናት ተፈሪ ገብረ እግዚአብሔር አጭር የሕይወት ታሪክ

መልአከ ብርሃናት ተፈሪ ገብረ እግዚአብሔር በትግራይ ራስ ገዝ በእንደርታ አውራጃ ደብረ ከዋክብት ዓዲዓቀይቲ በተባለ ቦታ ከአባታቸው ከመሪ ጌታ ገብረ እግዚአብሔር ገብረ ዮሐንስ ከእናታቸው ከወ/ሮ አመተ መኰንን በ፲፱፻፲፪ ዓ·ም ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በትግራይ ሀገረ ስብከት ባሉ ታላላቅ ገዳማትና አድባራት እየተዘዋወሩ ፡ ምዕራፍ ጾመ ድጓአቋቋም ቅኔ ፡ ዝማሬ ማዋሥዕት ፡ መዝገብ ቅዳሴ በሚገባ አጠናቅቀው ተማሩ ፡

ቀጥለውም ወደዙር አምባ (ዙር አባ) በመሄድ በዝማሬ መዋሥዕት ሙያ ተመረቁ ፡ ከዚህ በኋላም በአቋቋምና በመዝገብ ቅዳሴ ሙያ ተመርቀው በዝማሬ መዋሥዕት በምዕራፍ፡ ጾመ ድጓና በመዝገብ ቅዳሴ የማስተማር ሥራቸውን ቀጠሉ ።

መልአከ ብርሃናት ተፈሪ ገብረ እግዚአብሔር በትሩፋትና በመደበኛ አስተማሪነት ለ፳ ዓመታት ያገለገሉ አባት ሲሆኑ ከ፴ ያላነሱ ደቀመዛሙርትን አስተምረው ለከፍተኛ ሙያ አድረሰዋል ።

መልአከ ብርሃናት ተፈሪ ገብረ እግዚአብሔር በሙያቸው ጠንቃቃነት ፣ በግበረገብነታቸው (በትሕትናቸው) በድምፃቸውና በትጋታቸው ሁሉ በሊቃውንት ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትን ያተረፉ አባት ነበሩ ። በትጋታቸውም ቤተ ክርስቲያናችን እንደመሪ ጌታ ተፈሪ የመሰሉ ጥቂት ሊቃውንት ብታገኝ ታላቅ ጸጋ ነበር። በማለት በታላቁ አባት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የተነገረላቸውን የምስክርነት ቃል ማስታወሱ በቂ ይሆናል።



መ/ብርሃናት ተፈሪ ገ/እግዚአብሔር እኒህ ነበሩ

መልአከ ብርሃናት ተፈሪ የሚደነቁት በሙያቸውና በትሕትናቸው ብቻ ሳይሆን በክህነታዊ አለባበሳቸውም ጭምር ነበር ፡ በዚሁም የቤተ ክርስቲያናቸውን ክብርና ባህል የሚያስጠብቁ ፡ ለትውልድ የተሟላ አርአያነት ያለው ትምህርት የሚሰጡ ታላቅ አባት ነበሩ ።

እኒህ አባት በዚሁ ሙያቸው ሳይወሰኑ ባላቸው ትርፍ ጊዜ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ የሆኑ ሥራዎችን ከማበርከት አልቦዘኑም ሰበካ ጉባኤ ሲቋቋም የመቀሌ ስምንቱ አድባራት ሊቀ መንበር በመሆን ምእመናንንና ካህናትን በማስተባበር ለሰበካ ጉባኤና ለሰንበት ት/ቤት መጠናከር ያደረጉት ከፍተኛ ጥረት ምንጊዜም የሚዘነጋ አይደለም ። ሰበካ ጉባኤ ተጠናክሮ ትክክለኛ መስመር እንዲኖረው ካደረጉ አበው አንዱና ዋንኛው ከመሆናቸውም ሌላ የሰንበት ት/ቤቶች አባት ለመባልም ታድለዋል ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም አገልግሎታቸውንና ሙያቸውን በመመልከት መልአከ ብርሃናት ብላ በመሾም የደብረ አሚን አቡነ ተክለሃይማኖት አስተዳዳሪ ሆነው እንዲሠሩ ስለፈቀደችላቸው የደብር አስተዳዳሪነታቸውን ከማስተማር ሥራቸው ጋር ደርበው ሲያከናውኑ ቆይተዋል።

መልአከ ብርሃናት ተፈሪ ገብረ እግዚአብሔር የአንድ ወንድና የአራት ሴቶች አባት ሲሆኑ ምንም ትምህርት ደግነትና ትሩፋት ቢበዛ ሞት የማይቀር የሰው ልጅ ዕዳ በመሆኑ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ለብዙ ወራት ሆስፒታል ገብተው ሲረዱ ከቆዩ በኋላ በተወለዱ በ፸፫ ዓመታቸው ጥቅምት ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም የሞት ጽዋን ተቀብለው ጥቅምት ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም አዲስ አበባ በደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን ብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ የበላይ ኃላፊ በተገኙበት ተገቢው ጸሎተ ፍትሐት ተከናውኖ ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጽሞአል ። በሥርዓተ ቀብራቸው ከተበረከቱት ቅኔዎች የሚከተሉት ይገኙባቸዋል ።

<u>ከመልአከ ፀሐየ ሠምረ ክርስቶስ</u>

<u>፩ኛ ሥላሴ ቅኔ</u>

ውን ወደ ወይን ጠጅ እንደ ለወጠው ሁሉም በአመላከነቱ እመኑ ደቀ መዛሙርቱም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አመኑበት የሐ· ፪ ፲፩ ከዚህ ላይ ሦስት ጠቃሚ ነገሮችን እንረዳለን እነዚህም ፩ኛ የእመቤታችን አማላጅነት ምን ያህል ችግር እንደሚያስወግድ ፡

፪ኛ ጋብቻ ክቡርና ቅዱስ ሕግ መሆኑን ለማስገንዘብ ጌታችን ከሠርግ ቤት መገኘቱ

፫ኛ እመቤታችንም ሆነች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደስታችንና በመከራችን ከእኛ እንደማይለዩን ነው ።

ከነፈርግብ ማርቆስ

# እናስተዋውቃችሁ

፱ኛ ሐዋርያ ልናስተዋውቃችሁ የዘገጃጀንላችሁ ያቀረብነው በደቡብ ጎንደር ክፍለ ሀገር በጋይንት አውራጃ በስማዳ ወረዳ የሚገኘውን የጐሽ ሜዳ ቅዱስ ሚካኤልን ገቢረ ተአምራት ሥራዎች ነው የጐሽ ሜዳ ቅ.ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የተተከለው በ፲፩፻፸፱ ዓ.ም መሆኑን ታሪክ መዝገብ ዘቤተ ክህነት ተራ ቁጥር ፱፻፶፱ በሚገባ ታሪኩ ያስረዳል ። ስለዚህ የዚህን ታሪክና አመዘጋገቡን ይዘንላችሁ ቀርበናል ።

ይህ ቤተ ክርስቲያን አቀማመጡ ጐጃም ፡ ወሎ ፡ ሸዋ ፡ ወደሚገናኙበት ፡ ዓባይ ወንዝ አፋፍ ሲሆን ወደ ጐጃም መሻገሪያ መውረጃ ወደሸዋ ሲሄዱ መውረጃ ወደ ወሎ አምሃራ ሳይንት ሲሄዱ ማለፊያ ቦታ ሆኖ ከአፋፉ ላይ ለ፫ቱም ሀገሮች ትይዩ የሆነ ድንቅና አስደሳች ቦታ ነው ።

አካባቢው ታቦቱ የተተከለበትን ቦታ ይዞ እስከ ዓባይ ጐጃም ጐንቻ መድኃኔ ዓለም አፋፍ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጀምሮ ፩፻ ዘመን ድረስ ምንም ሰው እንደሌለበትና የአንበሳና የነብር በተለይም የጐሽ መናኸሪያ ቦታ እንደነበረ ተመዝግቦ የተገኘው ታሪክ ያስረዳል ።

በተለይም ከክርስቶስ ልደት በኋላ እስከ ፻፩ ዓመት ድረስ ታቦቱ የተተከለበት ቦታ እጅግ በጣም ጫካና ደን ስለነበረ በብዛት የጐሽ መዋያ እንደነበረ ይነገራል ። በኋላ ግን ሰዎች በአካባቢው መኖር ሲጀምሩ የዱር አራዊቶቹ እያለቁና እየሸሹ ሲሄዱ ደኑ ጫካው ወደ መጥፋት ላይ ሲደርስ በዚሁ ሜዳ ደን ብቻ ያለው ጐሽ ቀረ በኋላ ግን በዘመኑ ያቀናው የአብርሃ ወአፅብሐ ተከታይና ፲፰ኛው ንጉሥ የነበረው ቤተ እስራኤል የተባለው ንጉሥ አሽከር ካልዕ ጃን የተባለው ሀገሩን ሲያቀናና ሲመሠርተው በአካባቢው ያሉት የዱር አራዊቶች ሲሸሹ አንዱ ትልቅ ጐሽ አውሬ ብቻውን ዛሬ ቤተ ክርስቲያኑ ከተተከለበት መቅደሱ ከአለበት ላይ ቆሞ ሳይንቀሳቀስ ፫ ቀን ከቆየ በኋላ በዘመኑ እጅግ በጣም ባህታዊ የነበሩትና የታወቁት ጐጃም መርጡለ ማርያምን ለማየትና ለመሳለም ከመጡት አባ ተአምረ እግዚእ የተባሉ አባት ያዩትና ለትንሽ ጊዜ ቆመው ጐሹን ከተመለከቱት በኋላ ሲጠጉት ለቆላቸው ሲሄድ እርሱ ከቆመበት ቦታ ድንጋይ እንዲተከሉበት መልአከ እግዚአብሔር መጥቶ ሲነግራቸው ትንሽ ድንጋይ ተክለው ጐሹን እዚያው እንዳለ ትተውት ወደ ጐጃም ተሻግረው መርጡለ ማርያምን አይተው ፫ ወር ቆይተው በዚያው ቢመለሱ የተከሉትን ድንጋይ ተንተርሶ ጐሹ ሞቶ በመሐሉም ወይን በቅሎ አለምልሞ አገኙት ሆኖም መሽቶባቸው ስለነበር ከጐሹ ሬሳ አጠገብ አጋሙንና አጋሙን አገናኝተው ጐጆ ሰርተው ፫ ቀን አደሩ በዚያው ሌሊት መላኩ ቅዱስ ሚካኤል ተገልጾ ይህንን ባርከው ይላቸዋል እርሳቸውም ሊባርኩ ብድግ ሲሉ ፴፯ አንበሶች መጥተው የጐሹን ሬሳ ጐትተው ወደ አፋፍ ይዘውት ሲሄዱ ያያሉ በዚሁ ጊዜ በነገሩ ተደናግጠው ተመልሰው ተኙ መላኩ አሁንም ተገልጾ ትንሽ ተኛ አረፍ በል ይላቸዋል ። ደክሞአቸውና ፀሐይ አቃጥሎአቸው ስለነበረ ተኝተው ሳሉ ጐሹ ከሞተበት ድንጋዩን ከተከሉበት ቦታ ላይ ቤተ መቅደስ ተሰርቶ ቅዳሴ ሲቀደስ ያያሉ በዚህ ጊዜ መላኩም የታቦተ ቅ.ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን እንዲያሰሩ ይነግራቸዋል ። በዚህ ጊዜ የሚዳውን ግርማ የጐሹን ታሪክ ይመለከቱና ቦታውም ከአፋፍ ላይ ሆኖ ለጐጃም ፡ ለሸዋ ፡ ለወሎ፡ በግንባር የሚታይና የዓባይም ወንዝ ተጋድሞ እንደ አስፋልት መንገድ መስሎ ከ፩፻፶ ኪሎ ሜትር ያላነሰ ሲሄድ ስለሚታይ ሜዳ ስለሆነ ይህ ቦታ የጐሽ መዋያ ስለሆነ ጐሽ ሜዳ ይባል አሉት ይባላል ። በእውነቱ ያሬድ ያልረገጠው ቦታና ሀገር ያልተባረከ መሆኑ ቢነገርም የዓባይንም ፩፻፶ መንገድ ዕርቀት የሚያሳይ ቦታ መሆኑ

ቆሞት እምድንጋጼ
ወሊቱ ለአቤል መቅበርተ ሥጋ
ማዕከለ ዕጺያት አሃው እንዘ ታን
ቀዓዱ ዓይነ
እስሞ ርእየት መልአከ ልእልና
ዘለብሰ ብርሃነ
ባሕቱ መልአከ ዘተካየደ ኪዳነ
ዘምሰለ እግዚእ ወእግዚእነ
ይቤላ ለዝሕር እኀተኩልነ
ከመባእድ ኢይምስልኪ አነ

<u>፱ኛ/ ሥላሴ ቅኔ</u>

<u>ከመሪጌታ ማርቆስ</u>

ድንግል ደብረ መልአከ (ደብረ ጽጌ)
እምነ ብዙኃን ትትሌአሊ ፡ ኪዳነ
ማርያም እግዚእ ቀዳሚ ዘነጸረኪ ነጽሮ ፡
ኪያኪ እምጣነ ሐረየ ትኩኒ ማህደሮ፡
ኡራኤልሰ መልአከ ለዝንቱ
ኪዳነ ማርያም አፍቂሮ
ዲበ መንበሩ እስከ አንብሮ
ወገነተ ዮሐንስ ኄር ኢያዜክሮ
እስመ በዝ አወፈየ ክብሮ





www.ethiopianorthodox.org

ሲረጋገጥ ሀገሩ በታሪኩ አለመያዙ ያሳዝናል ። ምዕመናን የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ፡ ማስተዋል ነው የቦታውን አቀማመጥ የጐሹን አቀማመጥ የጐሹን አሟሟት የጐሹን ራሳ አንበሶች ጉትተው ወደ ገደል መውሰድ ተአምሩ ብዙ ነው ። ከዚህ በኋላ ባህታዊው ወዲያውኑ ለንጉሥ ቤተ እስራኤል ሄደው ነግረው ንጉሡም ስለተስማሙ ጃን ለተባለው ባለሟላቸው ታቦተ ሚካኤልን እንዲሰጣቸው አዘዘው ታቦተ ሕጉን ከተረከቡ በኋላ ቤተ ክርስቲያኑን እንዲያሠሩ ሰው እንዲሰጣቸው ለጃን ፪ኛ ነግረውት ጃንም ሃሳባቸውን ተቀብሎ ቤተ ክርስቲያኑን የሚሠሩ ሰዎችን ሰጣቸው እርሱም አብሮ እንዲሄድ መላኩ በህልም ነገረው ። እነርሱም ከዓባይ ወንዝ ውኃውን በአህያ እያጓዙ ትንሽ ቤተ መቅደስ ሰሩ ። የተሠራው ቤተ መቅደስ ለ፵ ዓመት ከቆየ በኋላ ባህታዊው ሞተው እዚያው ሲቀበሩበት ሌላ የሚያገለግለው ሰው ባለመኖሩ በባህታዊው የተሰራው ቤተ መቅደስ ፈርሶ ጠፋ ።

በኋላ ግን ብርሃነ ኢትዮጵያ የሆነው ቅ.ያሬድ የሸዋንና የወሎን የጐንደርን መገናኛና ዓባይም እንዴት እንደተመለሰ ጐጃምን እንደከበበውና እንደተጠማዘዘ ለማየት ሲወርድ ከቦታው ላይ ሲደርስ መላኩ ቅዱስ ሚካኤል ተገልጾ በዚህ ቦታ ላይ ቆሞ በከፍተኛ ድምፅ እንዲዘምር ሲነገረው ጐሽ ሜዳ አፋፍ ላይ ሆኖ "አዓባይ አይቴ ተሐውር..." የሚለውን መዝሙር ሲዘምር የሰሙት በጐጃምና በወሎ በሸዋ ያሉት አእዋፍ በረው ሄደው በአንድ ጊዜ ቅ.ያሬድን ፩ሺ፰፻ የተለያዩ አእዋፍ ከበውት አድርዋል ። በአጋጣሚ ስለ ያሬድ አእዋፍ አገልግሎት ሰጭነት ልንገልጽ የምንፈልገው ያሬድ እየዘመረ ሲሄድ በራሱ ላይ ክንፍና ክንፋቸውን አገጣጥመው ብዛታቸው ቀን ፲፪ አእዋፎች ፀሐይ እንዳይመታው ሌሊት ቁር እንዳያገኘው ፲፪ አእዋፎች ተጋርደውለት ይሄዱ ነበር ይላል በዚህ ደብር የእጅ ጽሑፍ የተገኘው ታሪክ በገጽ ፺ ላይ ያስረዳል ከዚያም በኋላ ሲነጋም ጧት የ፬ቱን ሀገር መገናኛና የዓባይንም ጉዞ አይቶ ሲመለስ ጐሽ ሜዳ አጠገብ ሲደርስ ዳገቱን ወጥቶ ሌሊት ያደረባትን ቦታ ሲያይ አእዋፎቹ በአማረ ድምጻቸውና በሚሰማቸው ቋንቋቸው በዚያ ቦታ እንዲያድርላቸውና እንዲዘምርላቸው ስለጠየቁት ማታ ምንድቅ በተባለው ቦታ ተቀምጦ ሳለ እግሩን የሚታጠብበት ቦታ ውኃ ስለሌለ መቋሚያውን ቢተክለው ውኃ ፈልቆ ወርዶ ዓባይ ገባ አካባቢውም ምን ድንቅ ነገር ተባለ እስከ አሁንም ድረስ ምንድቅ እየተባለ ይጠራል ። ምንጩም የያሬድ ምንጭ እየተባለ ለትንሽ ጊዜ ሲጠራ ከቆየ በኋላ ታሪኩን የሚያውቁት አባቶች ሲሞቱና ሲያልቁ ታሪኩ እየተረሳ ሄዶ ዛሬ የያሬድ ምንጭና ምንድቅ መባሉ ቀርቶ በሕዝቡ አነጋገርና ልማድ ምን ቁርቁርት ምንድቅ እየተባለ ይጠራል ። ታቦቱም አጠገቡ ካለው ሜዳ ላይ ለጥምቀት ወርዶ ፪ ቀን ያድርበታል እዚህ ላይ የምናስታውሰው ነገር ቢኖር የቦታውን ባለታሪክነትና የቅ.ያሬድንም ተአምር ሠሪነት ነው ። ለመሆኑ ቅ.ያሬድ ባይገኝ ኖሮ ዛሬ ያሉት መዘምራን ከምን ቦታ ይገኙ ነበር። ያሬድ ባያዜምላቸው እንዴት ሊታወቁ ይችሉ ነበር ። የያሬድን ውለታ ለአንባብያን እንተወውና አሁን ወደተነሳንበት ዓላማ እንመለስ በዚህም ምክንያት ከላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ በ፩ሺ፩፻፹፪ ዓ.ም. አሁን ያለው ቤተ ክርስቲያን ተተከለ ። ስለዚህ የጐሽ መዋያ ስለነበረ ጐሽ ሜዳ ቅ.ሚካኤል እየተባለ እንዲጠራ ባህታዊው በጽሑፍ በድንጋይ ላይ ጽፈው አስቀምጠውት ስለተገኘ የተጻፈውንም የድንጋይ ጽሑፍ የኋላ ሊቃውንት እያንዳንዳቸው ታሪኩን አስቀምጠውት ስለተገኘ እነሆ ዛሬ ጐሽ ሜዳ ቅ. ሚካኤል እየተባለ ይጠራል ። ይህም ቤተ ክርስቲያን ዛሬ በሳር ክዳን ከተሰራ ፰፻ ዘመን የሆነው ግንብ ተሠርቶ ሲያበቃ በያሬድ ደቀ መዝሙር ፯ኛ ልጅ በሆነው ልሳነ ዕፍረት በተባለው መዘምር ተመርቆ ገባ ይባላል ልሳነ ዕፍረት ታቦቱን ካስገባ በኋላ ተመልሶ ወደ ቤተ ልሔም ወጣ የጐሽ ሜዳ ቅ.ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንም የሚከበረው ኅዳር ፲፪ ቀን ብቻ ነው ። በዚህም ጊዜ በአካባቢው ያሉት ምዕመናን የማይደግስ እንግዳ የማይቀበል ማንም አይገኝም በቃል ከዳኑ መሠረት በጐሽ ሜዳ ያለው አንድ ትልቅ ፪፻ ዘመን ያለው መስቀል ሲወጣ የዛር ውላጅ ተያዥ ሚርት ጠቅላላ በሽታ ያለበት ሰው ሁሉ ይጮኽል ይንቀጠቀጣል ልብረር ልብረርም ይላል ይጥለዋል ያንፈራግጠዋል በመስቀሉ ሲታሽ ተፈውሶ ይሄዳል ። ለዚህም ነው ሐዋርያው የዓለም ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ በመልዕክቱ የመስቀሉ ነገር ለእኛ ለምናምነበት ። የእግዚአብሔር ኃይል ነው ለማያምኑት ግን ሞኝነትና ስንፍና ነው ያለው ስለ



ዚህ በጐሽ ሜዳ ቅ.ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ለተልዕኮ ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው ተቀድሶ ቤተ ክርስቲያኑ ከተዘጋ በኋላ በግቢው ውስጥ መዞር መውጣት ወደ ውስጥ ከአጥር ግቢው መግባት አይችልም በጉለበት ምን አለብኝ ብሎ ቢገባ ይታመማል እንደበቱ ይያዛል ሆኖም ዲያቆናት ለሥራ ሲሄዱ ግን የታወቀ ስለሆነ አይታመሙም ለአገልግሎት ስለሄዱ የሚነካቸው ነገር የለም ጠባቂው እራሱ ቅ.ሚካኤል ስለሆነ ቤተ ክርስቲያኑ እስከ ዛሬ ድረስ ከተተከለ ጀምሮ ተቆልፎ አያውቅም እንዲያው መለስ ነው የሚደረገው ከመቅደሱ ጀምሮ እስከ ቅኔ ማኅሌቱ ያሉት በሮች በሙሉ አይቆለፉም ማንስ ደፍሮአቸው ማንስ ከቅፅሩ ገብቶ ፡ ቢገባም ያለሥራው ከሆነ አይነቃነቅም ከጸሎትና ከሥራ በስተቀር፡ ይህ ነው ተአምር ማለት በከተማችን ያሉትን አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ቁልፋቸውን እየሰበሩ ሲሰርቁ በግቢውም የቁማር የሌላም መጫወቻ እያደረጉአቸው እናያለን ይህም ያሳዝናል እንዴት ለቤተ ክርስቲያን ሥጋዊ ዘበኛ ያስፈልገዋል ። ይህም የእምነት መጉደል ነው ። ሁሉም ታማኝ ቢሆን ኖሩ እንደጐሽ ሜዳ ቅ.ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ዘበኛ ባላስፈለገም ነበር ይህንንም ለአንባብያን ትተነው እናልፋለን ። የደረሰባችሁ አስተውሉት ።

የጐሽ ሜዳ ቅ.ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አሁንም ከ፫ሺ እስከ ፰፻ እድሜ ያላቸው የወይራ ፡ የዕድ ፡ የወርካ ፡ ዛፎች ይገኙበታል ። ትክል በቀል ድንጋዮች ይገኙበታል ። ከቤተ ክርስቲያኑ በራፍ ላይ ቆሞ ሲመለከቱ ዓባይ እንደ አስፋልት ሆኖ ሲሄድ ይታያል የጐሽ ሜዳ ቅ.ሚካኤል ደወል ሲደወል ጐጃም ፡ ሸዋ ፡ ወሎ በአሻጋሪ ሌሊት ይሰማል ጐሽ ሜዳ ቅ. ሚካኤል ሄዶ ሰው ታሞ በፀበል ሲጠመቅ በፀበል ተጠምቆና በመስቀሉ ታሽቶ ከሄደ ማንም በሽተኛ ይድናል ። ከዳነም በኋላ እዚያው በየወሩ ባይሄድ በበሽታው ተመልሶ ይታመማል።

፪ኛ በግራኝ ጊዜ ከግራኝ እንድናለን ያሉት ሰዎች ለመደበቅ ከመቅደስ እንገባለን ። ቢሉ መቅደሱ ተዘግቶ አልከፈትላቸው ብሎአል ፫ኛ ደግሞ በጣሊያን ጊዜ ሰዎች በመደፋፈር ያንን ፪፻ ዘመን ያለውን መስቀል ይዘው ሊሄዱ ሲሉ እጃቸውን ሽባ ዓይናቸውን ጨለማ ስላደረገባቸው ። ትተውት ሄደዋል ፬ኛ በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም ፫ ሰዎች ከጐጃም ፰ ከብቶች ሰርቀው ይዘው ሲሄዱ ባለቤቶቹ እየተከታተሉ ሲደርሱባቸው ሸሽተው ከብቶቹን ጥለው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሊገቡ ሲሉ መብረቅ ወርዶ ሌቦቹን ስለገደላቸው ከብቶቹ በቅፅሩ ውስጥ እንዲያድሩ አድርጐ መልአኩ በራዕይ ባለቤቶቹን እኔ እየጠበኩ ነውና ውሰዱልኝ ብሎ መርቶ ከብቶቹን አስረክቦአቸዋል ። እንግዲህ ስለጐሽ ሜዳ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክረስቲያን ለጊዜው በዚሁ ይብቃንና በሚቀጥለው ሌላ ታሪክ ልናስተዋውቃችሁ ተዘጋጅተናል እኛንም እናንተንም እንዲጠብቀን የአምላካችን ፈቃዱ ይሁን አሜን።

ሊቀ ብርሃናት መርቆሬዎስ አረጋ

## ጾማችሁ እንደ ግብዞች አይሁን

(ከገጽ ፳፪ የዞረ)

ፈሪሳውያን አይሁን ፡ ስለ ጽድቅ በምትሠሩት ሥራ ሁሉ እነርሱን አትምሰሉአቸው ማለት ነው ። ባጭር አባባልም ስለ ራስህ ሌሎች እንጂ አንተ አትናገር ማለት ነው (ምሳ. ፳፯፡፪፡ማቴ ፳፫፡፲፪)

"ራስህን ተቀባ" ስለሚለውም በምንም ዓይነት መንገድ ይሁን ራሳችንን እንድንቀባ አላዘዘንም። በዚህም ምክንያት ሁላችን የሕጉ ተላላፊዎች እንድንሆን አይደለም። ይልቁንም መኖሪያቸውን በዱር ፡ በገደል ፡ በጫካና በበረሃ ፡ በዋሻና በገዳም ላደረጉ ማኅበራነ መነኩሳት ከባድና የራስ ምታት የሆነውን ሸክም እንዳናሸክም ነው "እርሱ ያለው ይህ አልነበረም ። ይህም ይታወቅ ዘንድ የጥንት ሰዎች በሚደሰቱበት ጊዜ አዘውትረው የመቀባት ልምድ እንደነበራቸው ከዳዊትና ከዳንኤል ለመረዳት እንችላለን ። (፪ኛ ሳሙ. ፲፪፡፳፣ ዳን. ፲፡፫) እራሳችንን እንድንቀባ እርሱ ያዘዘው በእርግጥ እንድናደርገው አይደለም ። ነገር ግን ዓቅማችን በፈቀደልን መጠን በሚገባ እንድንጾምና በጾማችንም ከሌሎች ዘንድ ውዳሴ ከንቱን እንዳንቀበል መጠንቀቅ እንዳለብን ሲያስረዳን ነው እንጂ። ይህንም ለማመን እንዲቻል እርሱ ራሱ አርባ ቀናት ጾሞአል ። እርሱ ራሱን አልተቀባም ፡ እርሱ እራሱን አልታጠበም ፡ ይልቁንም ከሁሉ በላይ ያለምንም ግብዝነት ሁሉንም ፈጽሞአል ። በማለት ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ከማቴዎስ ወንጌል ም.፲፮ ላይ በመነሣት በሰጠው በ፳ኛው ቃለ ምዕዳን በግልጽ ራስን መቀባት አለመሆኑን ያብራራል ።

ይቀጥላል

ከመሪጌታ ፀሐይ ብርሃኑ
ኒው ወርክ



www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

## ካልተረዳዱ ኑሮ ከባድ ነው

"ሐምሳ ሎሚ ላንድ ሰው ሸክሙ ነው ለሃምሳ ሰው ጌጡ ነው" እንደሚባለው ሁሉ ኑሮንም ላንድ ሰው ብቻ ቢያሸክሙት ሸክሙ ይከብደዋል ። ተከፋፍለው ቢሸከሙት ግን ስለሚቀል ኑሮ ጣእምና በረከት ያለው ይሆናል ።

ይህንንም ያወቀው አምላካችን እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው "ገነትን ጠብቃት ተንከባከባት" እንዳለው እናገኛለን ። ይህም ብቻውን ሳይሆን ከረዳቱ ጋር እየተረዳዳ ይሥራ ማለት እንደሆነ ምሥጢሩ አይሰወርብንም ቀጥሎም ሥራ ጠቃሚ መሆኑን ሲያስተምረው ጥረህ ግረህ በላብህ ወዝ እንጀራህን ብላ ብሎታል።

እርሱም ከረዳቱ ጋር ትእዛዙን ተቀብሎ በመሥራት ኑሮውን አሻሽሏል ። በየጊዜው የተነሳውም ትውልድ የርሱን አርአያ ተከትሎ በመሥራት ላይ ይገኛል ። በመሆኑም ሴቶች በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰልፈው ግዴታቸውን በመወጣት ራሳቸውንና ቤተ ሰቦቻቸውን ያስተዳድራሉ ። ይህንንም ሲፈጽሙ በትዳር ዓለም ወይም ከወላጆች ጋር በመኖር ነው ።

በጋብቻ ዓለምም ላይ ሆነው ፍፁም የሆነ የቤተሰብ ፍቅር ሊያድርባቸውና የቤተሰባቸው ምሰሶ ማለት ቋሚ አስተዳዳሪዎች መሆን ይኖርባቸዋል ። ለዚህም የትዳር ጓደኛቸው ምክርና ሀሳብ መለየት የለበትም ። ይህ ካልሆነ ግን ኑሮአቸው በተስተካከለና በተሟላ አቋም አይካሔድም ።

ስለዚህ ተከባብረውና ተሳስበው መኖር ይፈለግባቸዋል ። በመሆኑም ባልና ሚስት ተናንቀው ሳይሆን ተከባብረው መኖር እንደሚገባቸው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ክርስቶስንና ቤተ ክርስቲያንን ምሳሌ አድርጎ አቅርቧል "ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጥቷልና ። እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደራሳቸው አድርገው ሚስቶቻቸውን ሊወዷቸው ይገባል ። ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳልና ማንም ራሱን የሚጠላ ከቶ የለም። ስለዚህም እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት" ብሏል ኤፌ ም ፭ ቁ ፳፭ ፴፫።

ይህንን የጻፈው ቅዱስ ጳውሎስ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለምን ሆን ለእኛ ለምዕመናንና ለምዕመናት እንደሆነ ክርስቶስ ራሱን አሳልፎ እንደሰጠልን እናውቃለን ፍጡሮቹን እንደራሱ አድርጎ ስለ ወደደን ፍቅሩን በመስቀል ላይ ገልጦልናል ። ቀጥሎ ደግሞ በጋብቻ ክቡርነት ላይ ያሉትን የባልና የሚስትም ፍቅር የተሟላ መሆን እንዳለበት ያስረዳል።

ስለዚህ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ይህን በመሰለ በመረዳዳት እየኖሩ የቤተሰብ ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው እንጂ የሆነ ያልሆነ ምክንያት እየፈለጉ ወንዶችም ሚስቶቻቸውን ባረጁ ጊዜ ወደሌላይቱ ተመልክተው መመንዘር እንደማይገባቸው ጠቢቡ ሰሎሞን እንዲህ ብሏል ።

"ከጕብዝና ሚስትህ ጋር ደስ ይበልህ እንደተወደደችም ዋልያ እንደተዋበችም ሚዳቋ በጡትዋ ሁልጊዜ ታርካህ በፍቅርዋ ሁልጊዜ ጥገብ እንጂ ስለምን ጋለሞታ ሴት ትወዳለህ ። የሌላይቱንስ ብብት ታቅፋለህ" ብሏል ። ምሳሌ ፭ ቁ ፲፰ ፳።

እንዳለውም ይህን የመሰለውን መልካም ዓላማ ትቶ ከሳቶ፤ ጠቆረች፤ ተመመች፤ ሰነፈች፤ ስሚል አጉል አስተሳሰብ ተነሥቶ የራሱን ሚስት በመተው ሌላይቱን ውበት ያላትን ፤ ሀብት ወገንና ዘመድ ያላትን መፈለግ ሕገ ወጥነት ከመሆኑም ሌላ የቤተሰብን ፍቅር የሚበክልና ትክክለኛ ያልሆነ ድርጊት በመሆኑ የትዳርም እንቅፋት ስለሆነ ይህንን ተገንዝቦ የልጅነት ሚስትን አክብሮ መያዝ ተገቢ ነው ።

በተጨማሪም ጠቢቡ ሰሎሞን ይህን ያለበት አንድ ምክንያት አለው ወንዱ በወጣትነቷ ጊዜ የአበባዋ ወራት ደምቆ ሁሉን በሚስብበት እና በሚማርክበት ሁሉም ላግባሽ እያለ በሚጠይቅበት የወጣትነት ዘመን አጭተህ ያገባሃትን ሚስት እንደ መጀመሪያው ወቅት ውደዳት ውበቷም መልኳም እንደ ጽጌረዳ አበባ መስላ ትታይህ እንጂ በሁለታችሁ መካከል ለውጥ አይኑር ሴቷም ብትሆን እንዲሁ ትመልከተው ማለቱ እንደሆነ ሊቃውንት አስተያየት ይሰጡበታል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች ጌጥ ወዳጅና ወረተኛ ማይሆኑ ያዩትን ሳይወዱ ቤተ ሰቦቻቸውንና ባሎቻቸውን ማክበር ይገባቸዋል ወረተኛና ጌጥ ወዳጅ መሆን የያዙትንም መሰልቸት ተገቢ እንዳልሆነ የአንዲት ሴትን ታሪክ እንመልከት ። ጌጥ የምትወድ አንዲት ሴት ነበረች ። በጣቷ ቀለበት ላይ የአንበሳ ምስል አሠርታ ታጌጥ ጀመረች ከጥቂት ቀን በኋላ ስለሰለቻት ያንበሳ ምስል በእጄ ተሸክሜ ምን ያደርግልኛል አለችና ያንን አስፈርሳ እንደገና በልዩ ልዩ ሐረግና ፈርጥ አሰርታ ማጌጧን ቀጠለች ። የዚህም ወረቱ ስላለቀላትና ስለሰለቻት የምትይዘውንና የምትጨብጠውን አጥታ ጨነቃት በመጨረሻም ከአንድ አንጥረኛ ዘንድ ሄደችና በሰው ዘንድ ሳየው ሁሉ ነገር ያስደስተኛል ። እኔ ራሴ ሳደርገው ግን ወዲያው ይሰለቸኛል ። የማይሰለች ነገር ምንድን ነው አለችና ጠየቀችው አንጥረኛውም ካህን ስለነበር የማይሰለች ክርስቶስ ብቻ ነው እርሱን ከልብ ብትወጂውና ቀለበትሽንም እርሱ የተሰቀለበትን የሥነ ስቅለት ምልክት ብታስቀርጭበት መንፈሳዊ ደስታ ከማግኘትሽም ሌላ ሁልጊዜ መከራውን እያስታወስሽ መስቀሉን ተሸክመሽ በኋላው ልትከተይው ትችያለሽ አላት እርሷም ነገሩ ስላስደሰታት ቀለበቷን እንደገና አስፈረሰችና በዚሁ ዓይነት አሠርታ እስከ ሕይወቷ መጨረሻ ድረስ ደስ ብሏት ትኖር ጀመር ይባላል ።

እንግዲህ ሴቶች የሆኑ ሁሉ የጌጥ ዓይነት የልብስ ሞድ በየጊዜው መለዋወጥ ፣ በገበያ ያሉትን ሁሉ ገዝቶ መምጣት ሲበዛ ያሰለቻል ። ለሴቶች የሚያስፈልጋቸው ነገር ቢኖር ኑሮ እንዳይሰለቻቸው ከሥራቸው መልስ የጓሮ አትክልትን መትከል ፤ በቤት አካባቢ አበባን ተክሎ ውኃ እያጠጡ እንዲያድግ መንከባከብ ፤ መጽሐፍ ማንበብና በማኅበራዊ ኑሮ በኩልም እየተገኙ ተሳታፊ መሆን ፤

ሥራንም ሠርቶ ከጨረሱ በኋላ የሥራ ልብስን ለውጦ አምሮና ተውቦ ባል ከሥራ ሲመጣ በፈገግታ ተቀብሎ በፈገግታ መሸኘት በበዓል ቀን ደግሞ ወደቤተ ክርስቲያን ሄዶ የጸሎቱና የቅዳሴው ተካፋይ ከሆኑ በኋላ ቅዱስ ቃሉን ሰምቶ ወደቤት መመለስ ኑሮን እንዳይሰለች ከማድረጉም በላይ ከረዳት ጋር ያፋቅራል ያስተባብራል ።

ስለዚህ ኑሮን የማይሰለችና የጣፈጠ እንዲሆን መተሳሰብ መከባበር ያስፈልጋል።

ወ/ት. መዓዛ አስማማው

## ጾማችሁ እንደ ግብዞች አይሁን

ጾም ማለት ከመብልና ከመጠጥ ለተወሰኑ ዕለታት መወገድ ብቻ ሳይሆን በብዙ መንገድ የሚፈጸም መንፈሳዊ ተግባር ነው ። ስለዚህም ክፉን ከመሥራት እጅን ፤ ክፉ ከመስማት ጆሮን ፤ ባልንጀራን ተናግሮ ከማስቀየም አንደበትን ፤ ተንኮልን ከማሰብ ልብን ፤ ወደ መጥፎ ቦታ ከመሔድ እግርን መከልከል ታላቅ ጾም ነው ። (ማቴ.፭፡፳) ጾም ፤ ጸሎት ፤ ምጽዋት ፤ እነዚህ ሦስቱ በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸው ሥራዎች ናቸው ። "አንድ ክርስቲያን ጾምን ከጸሎትና ከምጽዋት ጋር መፈጸም እንደሚገባው ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች። (ማቴ ፮፡፩ ፲፰) ጾም ለነፍስም ሆነ ለሥጋ እጅግ ጠቃሚ ነው ጊዜን ሳይወስኑ አዘውትሮ መብላት ደግሞ በሕይወት ላይ የጤና መታወክን ያስከትላል" ጾምን የሚጾም ማንኛውም ክርስቲያን እንደ አገኙ ከበላ ፤ እንደ አገኙ ከጠጣ ፤ ሰውነቱን ለመግታት ስለማይቻለው ለአካል ኃይልንና ልምላሜን ከሚሰጡ የምግብ ዓይነቶች ተከልክሎ ለተወሰኑ ወራትም ሆነ ሳምንታት ጾምን መጾም ይገባዋል ። (ዳን. ፲፡፫) ይልቁንም የአልኮል መጠጥ ልብን በመሰወርና አእምሮንም በማደንዘዝ ፤ በግል ሕይወት ላይ ጉዳትን ከማስከተሉም ሌላ፡ ከዚህም አልፎ ተርፎ ፤ መጥፎ ቃላትን የሚያናግርና እስከ ነፍስ ግድያም የሚያደርሱ ፤ የተለያዩ ወንጀሎችንም በማስፈጸም ከእግዚአብሔር መንግሥትም ሆነ ከኅብረተሰብእ የሚለይ፡ እጅንና እግርን እንደሰንሰለት አሥሮ ካልሆነ ቦታ ላይ የሚጥል፡ በግል ገንዘብ የሚገዙት አደገኛ የወዳጅ ጠላት ስለሆነ ጾምን የሚጾም አንድ ክርስቲያን ከዚህ ሁሉ መወገድ መንፈሳዊ ግዴታው መሆኑን ማወቅ ይገባዋል ። (ምሳ ፳፡ ፩፡ መሳ. ፲፫፡፫ ፬፡ምሳ.፳፫ ፴፩፡ ኢሳ. ፩፡፲፩ ፲፬)

በብሉይ ኪዳን የጾም መጀመሪያውና መሠረቱ በአራት ዘሌዋውያንና በአራት ዘኁልቁ (ዘሌ. ፲፮፡ ፳፱፡፳፫፡፳፯ ፳፱፡ ዘኁ. ፳፱፡፯ —፲፩) ስንመለከት የምናገኘው ነው ይህም ጾም በጥቅምት በሰባተኛው ወር ፤ ከወሩም በአሥረኛው ቀን እስራኤላውያን ሁሉ ሰውነታቸውን በማስጨነቅ በለቅሶና በኀዘን የሚጾሙት ፤ ከሠሩት በደል የሚነጹበት ፤ የንስሐ ሥርየትንም ከእግዚአብሔር የሚያገኙበት በመሆኑ የመጀመሪያውና ከሁ





www.ethiopianorthodox.org

ሉም አብልጠው የሚጠብቁት ጾም ነው ። (መዝ. ፻፳፰:፲፫ ፡ ኢሳ. ፶፰:፫,፭) ይህንንም ጾም እስራኤላውያን ብቻ ሳይሆኑ በእስራኤል የሚኖሩ ፡ ከእስራኤላውያን ጋር ምንም የነገድ ዝምድና የሌላቸው ባዕዳን ሁሉ እንዲጾሙት የታዘዘ ጾም ነው ይህ እንግዲህ በሙሴ የሕግ መጽሐፍ (ኦሪት) ተመዝግቦ የምናገኘው የመጀመሪያው ጾም ሲሆን ሌሎች ደግሞ በተለይም ዘመነ ፄዋዌን የሚያስታውሱ አራት አጽዋማት አሏቸው። እነርሱም ፡- ፩ኛ/ በ፭፻፹፯ ዓመተ ዓለም በአሥረኛው ወር (ከታኅሣሥ—ጥር) ስለ ኢየሩሳሌም መከበብ የሚጾሙት ጾም ፡ (፪ኛ ነገ ፳፭:፩፡ ኤር. ፴፱:፩፡)

፪ኛ/ በ፭፻፹፮ ዓመተ ዓለም የኢየሩሳሌም ቅጽር በባቢሎናውያን ስለመሰበሩ በአራተኛው ወር (ከሰኔ—ሐምሌ) የሚጾሙት ጾም፤ (፪ኛ ነገ ፳፭:፫—፲፩ ፡ ኤር. ፴፱:፪፡ ፶፪:፮,፯፡)

፫ኛ/ በ፭፻፹፮ ዓመተ ዓለም ስለ ጎልያድ መገደል በሰባተኛው ወር (ከመስከረም—ጥቅምት የሚጾሙት ጾም ፤ (፪ኛ ነገ. ፳፭:፳፭፡ ኤር. ፵፩ ፡ ፩—፫ ።)

፬ኛ/ የቤተ መቅደስን መቃጠል ምክንያት በማድረግ በአምስተኛው ወር (ከሐምሌ—ነሐሴ) የሚጾሙት ጾም ፤ በአጠቃላይ እነዚህ አራቱ አጽዋማት ናቸው። (፪ኛ ነገ ፳፭:፰—፱፡ ኤር. ፶፪:፲፪—፲፬፡) ስለ አራቱ አጽዋማትም በይበልጥ ለመረዳት ዘካ.ም ፯:፫፡ እና ፰:፲፱ መመልከት ይቻላል ። አምስተኛው ጾም ግን ጾመ አስቴር እየተባለ የሚጠራው ነው ይህም ፤ ከአራቱ አጽዋማት በኋላ ዘግይቶ የተጨመረው ፤ መታሰቢያነቱም በአስቴርና በመርዶክዮስ አማካይነት አይሁድ በሐማ ላይ ስለ ተጐናጸፉት ድል ሲሆን የሚጾመውም አደር ተብሎ በሚጠራው ከየካቲት እስከ መጋቢት ። (አስ. ፬:፫፡ ፺:፴—፲) ከሚጠት በኋላ ግን የብሉይ ኪዳን ጾም በሰፊው በሁሉም ዘንድ የተለመደ ሆነ ። (ዕዝ. ፰፡ ፳፩፡ነህም ፱:፩፡ማቴ. ፱:፲፬—፲፯፡ ሉቃ. ፪:፴፯:፲፰:፲፪)

የሐዲስ ኪዳን ጾም የተመሠረተው በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። ይህንንም ጾም እርሱ ራሱ በዮሐንስ ከተጠመቀ በኋላ በገዳመ ቆረንቶስ ብቻውን አርባ መዓልትና ፡ አርባ ሌሊት ፡ ጾሞ በሥራ በማሳየት ፡ በቃልም በማስተማር ፡ የመሠረተልን ስለሆነ ሁላችንም በሚገባ ልንጾመው ያስፈልገናል ጌታችን ይህንን ጾም። የጾመውም የፈጸመው በደል ኑሮ ሳይሆን በኛ ፋንታ የኛን በደል ተሸካሚና ስለ መተላለፋችንም ለሞት አልፎ የተሰጠ በመሆኑ ነው ስለዚህ እኛ ደግሞ የርሱን ፈለግ በመከተል ከጸሎትና ከምጽዋት ጋር ልንፈጽመው እንደሚገባን ለኛ ለማሳየት ነው ። (ማቴ. ፬:፩—፲፩ ፺:፩—፲፰፡ ኢሳ. ፶፫:፬—፭) በሦስቱ አርዕስተ ኃጣውእ ከዲያብሎስ በተፈተነ ጊዜም በገነት የመጀመሪያው አዳም ድል የሆነበትን ፈተና እርሱ ደግሞ ሁለተኛው አዳም በመሆን በገዳመ ቆረንቶስ እንደ አምላክነቱ ሳይሆን እንደ ሰውነቱ ዲያብሎስን ድል በመንሳት ለኛ የድል አክሊልን አቀዳጅቶናል ። ይህም ለከንቱ አይደለም ። እኛ ራሳችን ደግሞ የርሱን ትዕግሥቱንና ትሕትናውን የሕይወታችን መመሪያ በማድረግ ከማይታዩ ረቂቃን ጠላቶቻችን ጋር በምናደርገው ትግል በርሱ ፈተናን ድል ለማድረግ እንችል ዘንድ ነው ስለዚሁም ሐዋርያው ጳውሎስ ... ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለ ተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና ። "በማለት ያረጋግጥልናል ። (ዕብ ፪:፲፰) ቅዱስ ባስልዮስም ከዳዊት መዝሙር ፺:፩ ላይ በመነሣት በሰጠው ቃለ ምዕዳን በሞት ፍርድ ያለ ሰውን ሊያድንና ነፃም ሊያወጣ የሚችል አንድ ኃይል መኖሩን በመረዳት "በአንተ ታምኛለሁና አድነኝ ፡ ከችሎታዬ ማነስ የተነሣም ወድቂ የዲያብሎስ ምርኮኛ ከመሆን ነፃ አውጣኝ" በማለት ይጸልያል ። እንደዚህ ዓለም ምርጥ የስፖርት ተወዳዳሪዎችም መላ ዘመናቸውን ከማይታዩ ጠላቶቻቸው ጋር ሲታገሉ የሚኖሩ የእግዚአብሔር ምርጥ ቅዱሳንም ውድድራቸውን ጨርሰው ወደ ሕይወታቸው ፍጻሜ ሲደርሱ በዚህ ዓለም ገዥ (ዲያብሎስ) ይፈተናሉ ። በትግላቸው ጊዜ የደረሰባቸው የአካል መቁሰል (ኃጢአት) ቢገኝባቸው እሥር ቤት ይገባሉ ። ነገር ግን የሚያሳፍር ምንም የአካል ጠባሳ (ኃጢአት) ካልተገኘባቸው ግን የሁሉም ገዥ በሆነው በክርስቶስ ተከብረው በከፍተኛው ደረጃ ያርፋሉ ። በማለት ምን ጊዜም ጠላታችን ዲያብሎስ ለምንፈጽመው መልካም ሥራ ሁሉ ከፊታችን አሽክላውን ለመጣል ወደ ኋላ ስለማይል ተዘናግተን በወጥመዱ እንዳንገባና ከአምላካችን ጸጋ እንዳንጓደል የቂሣርያው ቅዱስ ባስልዮስ ያስተምረናል ።

ጾም ማለት ሥጋዊ ፍላጎታችንን የምናደክምበት ፤ መንፈሳዊ ኃይላችንን የምናጠነክርበት ረቂቅ ኃይል ማለት ነው ጾምን ስንጾም ሌሎች እንዲያውቁልንና ምስጋናን ከሰዎች ዘንድ ለማግኘት እንደ ማስታወቂያ አድርገን መጠቀም ተገቢ አለመሆኑን መድኃኒታችን "ስትጦሙ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ" ፤ በማለት ማቴ. ፮:፲፮ ላይ ያስተማረንን ማስታወሱ ይጠቅመናል ። ይህም ማለት ጦማችሁ እንደ ግብዞች

(ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል)



# ሒዱና አስተምሩ

ይህ የተቀደሰ ትእዛዝ የተሰጠው ለሐዋርያት እንደሆነ ግልጽ ነው ። ትእዛዙንም የሰጠው የዓለም መድኃኒት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ቀኑም ከትንሣኤ በኋላ እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል። ይህ ትእዛዝ የደረሳቸው ሐዋርያት ለጊዜው ከባድና አስቸጋሪ መስሎ ሳይታያቸው የቀረ አይመስልም ። ነገር ግን ትእዛዙን የሰጣቸውን መድኃኒታችን በሥራ ላይ ለማዋል ከመነሳታቸው አስቀድሞ የሚያስፈልጋቸው እንዳለ በማወቁ ያንን ሰማያዊ ኃይል እስከሚለብሱ ድረስ ሥራቸውን እንዳይጀምሩ ነግሯቸው ነበር። ያ ኃይል ምን ነበር የተባለ እንደሆነ በበዓለ ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስን መቀበላቸው ነው ። ከዚህ በኋላ ግን ምንም ሳይፈሩና የድንጋጤ መልክ ሳይታይባቸው በኃያላን ነገሥታት ፊትም ሆነ በአረማውያን መካከል እየተዘዋወሩ በማስተማር የክርስቶስን ቅዱስ ቃል በዓለም መስክረው አልፈዋል ።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ጰራቅሊጦስንና የሐዋርያትን ዝርዝር ሁኔታ ለማቅረብ ሳይሆን በየዘመኑ የሐዋርያትን አብነት ተከትለው ለማስተማር የሚነሱትን መምህራንና የሥራ ፍሬ ምን እንደሚመስል ለመግለጽ ሳይሆን በሥራ ምክንያት ነ፤ ፳ ከነበረበት በአሰብ ሀገረ ስብከት በሚገኘው በሐመረ ኖኅ ቅ/ሚካኤል ገዳም ያለውን ሁኔታና የምእመናኑን የትምህርት አቀባበል በተመለከተ የቀረበ መሆኑን አንባብያን እንድትረዱልኝ እፈልጋለሁ። በአሰብ ሀገረ ስብከት ሐመረ ኖኅ ቅ/ሚካኤል ገዳም ከሰኔ ሐምሌ ፲፱፻፸፪ ዓ.ም ድረስ በቅዳሴና በመምህርነት እንዳገለገል ከስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ በደረሰኝ የሥራ ድልድል መሠረት በቆየሁባቸው ጊዜያት ከሀገረ ስብከቱና ከሰሜን ወሎ ሊቀ ጳጳስ ከሆኑት ከብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በሚሰጠኝ መመሪያ ከካህናቱና ከምእመናኑ ጋር የተደረጉ መንፈሳውያን እንቅስቃሴዎችን ያካተተ ጽሑፍ ቀርቧል ።

የደብሩ ካህናት የአካባቢው የአየር ሁኔታ ማለትም የፀሐዩ ቃጠሎ የሙቀቱ ዓለትና በአጠቃላይም የበረሃውን ፀባይ በመቋቋም የተለመደውን ግልጋሎታቸውን በሚገባ ሲያከናውኑ መመልከቱ የሚያስደንቅ ነው ። በተለይም ምእመናኑ በሀገረ ስብከቱ የሚገኘው ቤተ ክርስቲያን አንድ ብቻ በመሆኑ በአጥቢያም ሆነ ከሩቅ አካባቢ ተጉዘው በመምጣት የክርስቶስ ቅዱስ ቃል ሲሰበክ የሚታይባቸው ተመስጦ እና ልዩ ፍቅር ይህ ነው አይባልም ።

ቢሆንም "ወጡ ሲገኝ እንጀራው አይገኝ" እንደሚባለው አንዳንድ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ተሟልተው ባለማየታችን አቅም በፈቀደ መጠን ከምእመናኑ የገንዘብ አስተዋጽኦ በመጠየቅ የክርስቲያኖች መንፈሳዊ ሕይወት አካሄዱ ሁሉ የተቃናና የተስተካከለ ሆኖ እንዲገኝ የሚከተለውን ዝርዝር ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ከብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ከሰበካ ጉባኤው ፡ ከማኅበረ ካህናትና ከሰንበት ት ቤት ተማሪዎች ጋር በመተባበር በተግባር ላይ እንዲውል ሆኗል ።

፩ኛ በተወሰነው ፕሮግራም ቀሳውስትና ዲያቆናት የደብረ ዓባይ መዝገበ ቅዳሴ ወንበር ተዘርግቶ የቅዳሴን ዜማ ከነሥርዓቱ በማስተማር የቀሳውስቱና የዲያቆናት ሙያ ተሻሽሎ ለቤተ ክርስቲያን ጥሩ አገልግሎት እንዲያበረክቱ በማድረግ ።

፪ኛ/ እሁድ እሁድ በየሳምንቱና በየበዓላቱ ሕዝበ ክርስቲያኑ ተሰብስቦ በሚሰጠው ትምህርት ራሱን እንዲለውጥና የቅዱስ ቃሉ ተካፋይ እንዲሆን ያለማቋረጥ በመሰበክ ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ፡

፫ኛ/ በገዳሙ በሚገኘው የጸበል ቤት "ለመጠመቅ የሚመጡ ምእመናንን የሚያስተናግድ ወንበር ባለመኖሩ አግዳሚ መቀመጫዎች ተሠርተው ተጠቃሚው ሕዝበ ክርስቲያን እንዲገለገልባቸውና ከደዌያቸው ለመፈወስ የሚመጡ ህመምተኞች ከመጠመቃቸው በፊት ጽኑ እምነት እንዲያድርባቸው የሃይማኖት ትምህርት በማስተማር በኋላም ለእምነታቸው ማጠናከሪያ የስብከተ ወንጌል ትምህርት ይሰጥበታል ።

፬ኛ/ ከጸበል ቤቱ ይፈስ የነበረው ውኃ ያለአገልግሎት እንዳይቀር በዚያው የሚገኙ የደብሩ ካህናትን በማስተባበር የልማት ተግባር እንዲያከናውኑ አትክልት በመትከል ካህናት የትርፍ ጊዜያቸውን በዚሁ ላይ እንዲያውሉ ሆኗል ።

፭ኛ/ የካህናት ኑሮ እንዲሻሻል ማለት የዲያቆናት ደመወዝ ብር ፪፻ የቀሳውስት ደግሞ ፫፻ ብር እንዲደርስና በተጣለባቸው የሥራ ምድብ ግዴታቸውን አውቀው በሞራል እንዲያገለግሉ ምክር በመስጠት ይህንና ይህን የመሳሰለውን ተግባር በምናከናውንበት ጊዜ ሁሉ ከአጠገባችን ሳይለዩ በሚሰጡን መንፈሳዊ መመሪያና



www.ethiopianorthodox.org

ሐሳብ እንዲሁም የምክር ድጋፍ ያደረጉልንን የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስን በእግዚአብሔር ስም ምስጋና ሳናቀርብላቸው አናልፍም ።

እንግዲህ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ "ሒዱና አስተምሩ" የሚለው ትእዛዝ ለደቀ መዛሙርቱ ብቻ ሣይሆን ዛሬም በዘመናችን ያሉትን ሐዋርያት የሚመለከት በመሆኑ መምህራንና ምእመናን አንድ ልብ አንድ ሐሳብ ሆነው በመገኘት ለቃሉ መዳረስ ከቃለ እግዚአብሔር ረሀብ ሰዎች ሊድኑና ሊገላገሉ የሚችሉበትን ዘዴ መሻት ይኖርባቸዋል ። ይህም ሲባል መምህራኑ ለሕዝበ ክርስቲያኑ የሚያቀርቡት መንፈሳዊ አገልግሎት የተሟላ እንዲሆን የምእመናኑ ትብብር አስተዋጽኦ አለውና ነው ።

በዮሐንስ ወ.ም ፬—፴፮—፴፰ "የሚዘራና የሚያጭድ አብረው ደስ ይላቸዋል የዘላለም ሕይወት ፍሬንም ይሰበስባሉ አንዱ ይዘራል አንዱም ያጭዳል በዚህ እውነት ሆኗልና እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ ሌሎች ደከሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ" ይላል በሚዘሩ የተመሰሉ ነቢያት ሲሆኑ በአጫጆች የተመሰሉ ደግሞ ሐዋርያት ናቸው ነቢያት የጌታችንን መውረድ መወለድ ትንቢት ቢናገሩ ሐዋርያት ከዘመኑ ደርሰው ወረደ ተወለደ ብለው አስተምረዋል መሠረት አድርገው የተነሱት ግን ክርስቶስን በመሆኑ ያቀዱት ዓላማ ተከናውኖላቸዋል ። ዛሬም የምእመናንና የአስተማሪዎች መሠረት ራሱ በመሆኑ በክርስቶስ ያመንን ሁላችን ስለክርስቶስ አዳኝነት የመመስከር ኃላፊነት አለብን ። በተለይም የወንጌል መምህራን የሆን በሉቃ ም፲፯ ቁ ፲ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል "በሉ ሲል ጌታችን የተናገረውን ቃል ተግባራዊ በማድረግ ለማያልፍ ዘላለማዊ ክብር የምንበቃበትን ትምህርት ማጠናከር ይፈለግብናል ።

አባ ተወልደ መድኅን ገ/ሥላሴ

## ጤናችን

### ያለ መድኃኒት ማዳን

ለአብዛኞዎቹ የሕመም ዓይነቶች ምንም ዓይነት መድኃኒት መጠቀም አያስፈልግም ። ሰውነት በተፈጥሮ በሽታን የመከላከልና የማሸነፍ ኃይል አለው ። ጤንነትን ለመጠበቅ አብዛኛውን ጊዜ ይህ በተፈጥሮ በሽታን የመከላከልና የማዳን ኃይል ከመድኃኒት ይልቅ የተሻለና የበለጠ ነው ።

ሰዎች ከጉንፋን ከኢንፍሉዌንዛና ከሌሎች አንዳንድ ሕመሞች ያለምንም ዓይነት መድኃኒት ከሕመማቸው የመዳን ኃይል አላቸው።

የሰው አካል በሽታን ለመከላከል ወይም ለመቋቋም እንዲቻል ለማድረግ የሚያስፈልግ ቢኖር ፩/ንጽሕናን መጠበቅ ፪ በቂ ዕረፍት ፫/ጥሩ ምግብ ናቸው በሽታው ከባድ ሆኖ ለመዳን መድኃኒት የሚያስፈልግ ቢሆንም እንኳ በሽታውን በይበልጥ የሚያጠቃውና የሚከላከለው የሰውነት የተፈጥሮ ኃይል ነው ። መድኃኒት ግን ተጨማሪ ረዳት ይሆናል ።

የግል ንጽሕና በቂ ዕረፍትና የተመጣጠነ ምግብ እጅግ በጣም ጠቃሚዎች ናቸው ።

አብዛኛውን ጊዜ የጤና አጠባበቅ ዘዴ በመድኃኒቶች ፈዋሽነት ላይ ትኩረት ሊኖረው አይገባም አንድ ሰው በሚኖርበት አካባቢ ምንም እንኳ ዘመናዊ መድኃኒቶች ባይኖረውም ቅሉ በርካታና ታዋቂ በሽታዎችን በመከላከልም ሆነ በማዳን ረገድ ከፍተኛ ተግባር ለማከናወን ይቻላል ።

ብዙ ዓይነት ሕመሞችን ለመከላከልና ያለምንም መድ ኃኒት ለማዳን ይቻላል

ሰዎች ስለበቂና ን ጹሕ ውሃ ማግኘት ዘዴና ትክክለኛ አጠቃቀም ከተማሩ ይህ ብ ቻውን እንኳን አሁን በአግባቡ ሆነ አለአግባብ በጠቀሜታ ላይ ከሚገኙት መድኃኒቶች በበለጠ ሕመሞችን ለመከላከልና ለማዳን ያስችላል ።

### በውሃ ማ ዳን

ብዙዎቻችን ያለመድኃኒት መኖር እንችላለን ። ነገር ግን ማንም ሰው ያለውሃ ሊኖር አይችልም የሰው አካል ክብደት ከግማሽ በላይ (ሃምሳ ሰባት ከመቶ) የሚሆነው ውሃ ነው ።እያንዳንዱ ሰው በቂና ንጹሕ ውሃ በአግባቡ ቢጠቀም በሰው ል ጆች ላይ የሚደርሰውን በተለይም የሕፃናት ሕመምና ሞት መጠን በግማሽ ሊቀንስ ይችላል ።

መል አከ ሕይወት
አባ ይ ትባረክ ዓለሙ

ይቀ ጥላል





# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ። ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቁ.
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org